ያቀናሉ፤ ወይነብሩ፡ ውስቴታ፡

ተሐንፁ፡ ቤተ፡ ወኢትነብሩ፡ ብሎ፡ ነበርና፡ በኢየሩሳሌም፡ ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ ተዘል ሰው፡ ይኖራሉ፤

ወይተክሉ፡ ወይነ፡ ወይሰትዩ፡ ወይኖሙ፤

ትተክሉ፡ ወይነ፡ ወኢትሰትዩ፡ ብሎ፡ ነበርና፤ ወይኑን፡ ይተ ክላሉ፤ ይጠጣሉ፤

ወይተክሉ፡ አዕፃዳተ፡ አቅማሕ፡ ወይ በልዑ፡ ፍሬሁ፤

ተክል፡ በሚተክሉበት፡ ቦታ፡ ሁሉ፡ ልዩ፡ ልዩ፡ የሆነ፡ ተክል፡ ይተክላሉ፤ ፍሬውን፡ ይበላሉ፤

፲፭፤ ወእተክሎሙ፡ ውስተ፡ ምድሮሙ፤

በሀገራቸው፡ አጸናቸዋለሁ፤

ወአልቦ፡ እንከ፡ ዘያወጽኦሙ፡ እምድ ሮሙ፡ እንተ፡ ወሀብክዎሙ፡ አነ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ዘኵሉ፡ ይመልክ፤

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እኔ፡ ከሰጠኋቸው፡ አገር፡ የሚ ያስወጣቸው፡ የለም አለ፤

ተፈጸመ፡ ዘአሞጽ፡ ነቢይ፡ በረከተ፡ አምላኩ፡ ትኩን፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤

ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፡ አሜን፡፡

# ዘሚክያስ ነቢይ

## መቅድም

ሚክያስ፡ ማለት፡ መኑ፡ ከማከ፡ መኑ፡ ከመ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው፤ ትውልዱ፡ ከነገደ፡ ብንያም፡ ነው፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ወኮነ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ኀበ፡ ሚክያስ፡ ነቢይ፡ ወልደ፡ ሞራት፤

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ ከሞራት፡ ልጅ፡ ከሚክያስ፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚ አብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤

በመዋዕለ፡ ያዝያን፡ ወኢዮአታም፡ ወአ ካዝ፡ ወሕዝቅያስ፡ ነገሥተ፡ ይሁዳ፤

እሊ፡ ነግሡ፡ በይሁዳ፤ እሊ፡ ነግሡ፡ ለይሁዳ፡ ይላል፤ በይ ሁዳ፡ በነገሡ፡ በነዚህ፡ ዘመን፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብ ሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ ስለ ምን፡ እነዚህን፡ አነሣቸው፡ ቢሉ፤ በነዚህ፡ ዘመን፡ ብመክ ራቸው፡ ባስተምራቸው፡ አንሰ ማም፡ ብሰው፡ ጠፉ፡ ለማለት፤

ዘርእየ፡ በእንተ፡ ሰማርያ፤

ሰማርያ፡ እንድትጠፋ፡ ዓይቶ፤

ወበእንተ፡ ኢየሩሳሌም፤

ኢየሩሳሌምም፡ እንድትጠፋ፡ ዓይቶ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤ አንድም፡ አሥሩ፡ ነገድ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ እንዲማረኩ፡ ዓይቶ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ይህ ነው፤

፪፤ ስምዑ፡ አሕዛብ፤

አሕዛብ፡ ስሙ፤

ወታፅምዕ፡ ምድር፤

ምድርም፡ ትስማ፡ ማለት፡ የተ ከሉባትን፡ አታጽድቅ፡ የዘሩባ ትን፡ አታብቅል፤

ወኵሎሙ፡ እለ፡ ይነብሩ፡ ውስቴታ፤

በውስጧ የሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ይስሙ፤

ወይከውነክሙ፡ እግዚአብሔር፡ ሰማዕተክሙ፤

እንሰማም፡ ብትሉ፡ እግዚአብ ሔር፡ ምስክር፡ ይሆንባችኋል፤

ደብረ ታቦር ... ቤተ ክርስቲያን የግል ቤተ መጻሕፍት

www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርሰ፡ ውስተ ቤተ፡ መቅደሱ።

እግዚአብሔር፡ ግን፡ በመመስገኛው፡ ቦታ፡ በጽርሐ፡ አርያም፡ ይኖራል፡ ማለት፡ ያውቅባችኋል፤

፫፤ ናሁ፡ እግዚአብሔር፡ ይወጽእ፡ እምቤቱ።

እነሆ፡ እግዚአብሔር፡ ከሰማይ፡ ይመጣል፤

ወይወርድ፡ መልዕልተ፡ ምድር፤

ወርዶ፡ በኢየሩሳሌም፡ ይቀመጣል፤

፬፤ ወያንቀለቅሉ፡ አድባር፡ በታሕቱ።

በዚህ፡ ዓለም፡ ከሰማይ፡ በታች፡ ያሉ፡ ተራሮች፡ ይነዋወጣሉ፡ ማለት፡ ነገሥታቱ፡ ይጠፋሉ፤

ወይትመሰዉ፡ አውግር፡ ከመ፡ ሰምዕ፡ ዘእምቅድመ፡ ገጸ፡ እሳት።

ከእሳት፡ የተነሣ፡ ሰም፡ ቀልጦ፡ እንዲጠፋ፡ መኳንንቱ፡ ይጠፋሉ፤ አንድም፡ ጌታ፡ በደብረ፡ ሲና፡ መጥቶ፡ በቆመ፡ ጊዜ፡ አድባር፡ ሙሴ፡ አሮን። አውግር፡ ሰብአ፡ ሊቃናት፡ ይነዋወጣሉ፤ አንድም፡ ጌታ፡ በቀራንዮ፡ መጥቶ፡ በቆመ፡ ጊዜ፡ አጋንንት፡ መናፍቃን፡ ይነዋወጣሉ፤ አንድም፡ ጌታ፡ መጥቶ፡ በደብረ፡ ጽዮን፡ በቆመ፡ ጊዜ፡ ተራሮች። ከረቢታዎች፡ ያልፋሉ፤

ወከመ፡ ማይ፡ ዘይውኅዝ፡ እምአድባር፡ በተታልዎ።

ከተራራ፡ ቀጥሎ፡ ቀጥሎ፡ እንደሚወርድ፡ ውሀ፡ ቀጥሎ፡ ቀጥሎ፡ መከራ፡ መጥቶባቸው፡ ይጠፋሉ፤

፭፤ ዝንቱ፡ ኵሉ፡ ዘይከውን፡ በእንተ፡ ኃጢአቱ፡ ለያዕቆብ።

ይህ፡ ሁሉ፡ የሚደረግ፡ በያዕቆብ፡ ኃጢአት፡ ምክንያት፡ ነው፤

ወበእንተ፡ ጌጋዮሙ፡ ለቤተ፡ እስራኤል።

ስለ፡ እስራኤል፡ ወገኖች፡ በደል፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ይደረጋል፤

ምንትኑ፡ ኃጢአቱ፡ ለያዕቆብ።

የያዕቆብ፡ ኃጢአቱ፡ ምንድ፡ ነው?

አኮኑ፡ ሰማርያ።

ሰማርያ፡ አይደለችምን፡ የዘሩባትን፡ ብታበቅልላቸው። የተከሉባትን፡ ብታጸድቅላቸው፡ አይደለምን፤

ወምንትኑ፡ ጌጋዮሙ፡ ለቤተ፡ ይሁዳ።

የሁለቱስ፡ ነገድ፡ በደላቸው፡ ምንድ፡ ነው?



ኢኮኑ፡ ኢየሩሳሌም።

ኢየሩሳሌም፡ አይደለችምን? የዘሩባትን፡ ብታበቅልላቸው። የተከሉባትን፡ ብታጸድቅላቸው፡ አይደለምን፤

፮፤ ወእሬስያ፡ ለሰማርያ፡ ከመ፡ ልገተ፡ ዓቃቤ፡ ቀምህ፡ በገዳም።

ሰማርያን፡ በምድረበዳ፡ እንዳለ፡ እንደፍሬ፡ ጠባቂ፡ ጎጆ፡ አደርጋታለሁ። ፍሬ፡ ጠባቂ፡ ፍሬውን፡ ለቅሞ፡ ጎጆውን፡ አፍርሶ፡ እንዲሄድ፤

ወከመ፡ ተክለ፡ ወይን።

እንደወይን፡ ጠባቂ፡ ጎጆ፡ ትሆናለች። ያ፡ እንዲፈታ፡ ትፈታለች፤ አንድም፡ ወይኑን፡ በክረምት፡ ግዘፍ፡ እንዲነሣ፡ ብለው፡ ከመሬት፡ እንዲጥሉት፡ በመከራ፡ እጥላቸዋለሁ፤

ወእነሥቶ፡ ለዕበኒሃ፡ ወአንህሎ።

ደጅዋን፡ አፈርሰዋለሁ፤ አንድም፡ አርበኛዋን አጠፋዋለሁ፤

ወእነሥት፡ መሠረታቲሃ።

መሠረቷንም፡ አፈርሰዋለሁ፤ አንድም፡ አርበኛዋን፡ አጠፋዋለሁ፤

፯፤ ወይሰብሩ፡ ኵሉ፡ ግልፎሃ።

የተቀረጸው፡ ጣዖቷ፡ ሁሉ፡ ይጠፋል፤

ወይውኢ፡ በእሳት፡ ኵሉ፡ ደነሳ።

አስበ፡ ዝሙቱ፡ ነው፡ የምትለው፡ ሁሉ፡ ይጠፋባታል፤

ወአጠፍዕ፡ ኵሎ፡ ጣዖታ፡ ምስለ፡ ደነሰ፡ ዝሙታ።

ጣዖቷን፡ አስበ፡ ዝሙቴ፡ ነው፡ ከምትለው፡ ጋራ፡ አጠፋዋለሁ፤

ዘአስተጋብአቶ፡ ለደነሰ፡ መሐዛኒሃ፤

ለወዳጆቿ፡ የሰበሰበችውን፡ ሁሉ፡ አጠፋዋለሁ።

ወተገበረት።

የደከመችበትን፡ ገንዘቧን፡ ሁሉ፡ አጠፋዋለሁ፤

፰፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ትበኪ፡ ወትላሁ፡ ወተሐውር፡ ዕራቃ፡ ዘእንበለ፡ አሣዕን።

ስለዚህ፡ ነገር፡ ታዝናለች። ታለቅሳለች። ያለ፡ ጫማ፡ ባዶዋን፡ ተማርካ፡ ትሄዳለች፤

ወትበኪ፡ ከመ፡ ከይሲ።

እንደእባብ፡ ቃሏን፡ አቅጥና፡ ታለቅሳለች፤

ወትላሁ፡ ከመ፡ አዋልደ፡ ሴርናን።

እንደ፡ ሰጎን፡ ገላግልት፡ ታለቅሳለች፤

www.ethiopianorthodox.org

፱፤ እስመ፡ ጸንዓ፡ መቅሠፍታ፤

መከራዋ፡ ስለጸናባት፤

እስመ፡ መጽአት፡ እስከ፡ ይሁዳ፤

እስከ፡ ይሁዳ፡ ድረስ፡ መጥ ታለችና፤

ወበጽሐት፡ እስከ፡ አንቀጸ፡ ሕዝብየ፡ ወእስከ፡ ኢየሩሳሌም፤

እስከ፡ ወገኖቼ፡ በር፡ እስከ፡ ኢየሩሳሌም፡ ደርሳለችና፤ በፋ ቍሄ፡ ጊዜ፤

፲፤ ኢትዘኃሩ፡ ሰብአ፡ ጌት፤

እስራኤል፡ አትታበዩ፤

ወኢትሕነው እለ፡ ውስተ፡ አቂም፡ ቤተ፤

በኃያላኑ፡ ቦታ፡ ያለ፡ አምባ ውን፡ አትሥሩ፤ አቂም፡ ስመ፡ ሀገር፡ ነው፤ አንድም፡ በአቂም፡ የምትኖሩ፡ አምባ ውን፡ አትሥሩ፤

ሐመደ፡ ደዩ፡ ውስተ፡ ርእሱ፡ ለኃሣርክሙ፤

በጣዖቱ፡ ላይ፡ አመዱን፡ ጣሉ፡ ማለት፡ ኀሡር፡ ነህ፤ ጕስቍል፡ ነህ፡ በሉት፤

፲፩፤ እስመ፡ ትመጽእ፡ ሠናይት፡ እንተ፡ ትነብር፡ ውስተ፡ አህጉሪሃ፤

በሀገሯ፡ በተድላ፡ በደስታ፡ የምትኖር፡ ቤተ፡ እስራኤል፤

ወተሐልፍ፡ እንተ፡ ትነብር፡ ውስተ ሰናየር፤

በሀገሯ፡ ጸንታ፡ ትኖር፡ የነበ ረች፡ ቤተ፡ እስራኤል፡ ወደ፡ ሰናየር፡ ተማርካ፡ ትሄዳለች፤

ወይበክዩ፡ አብያት፡ ዘጎሬ፤

የጐረቤቷ፡ ቤቶች፡ ያዝናሉ፡ የሰዎችን፡ ለቤቱ፡ ሰጥቶ፡ ተናገረ፤

ወይነሥኡ፡ እምኔክሙ፡ በመቅሠፍት፡ ወበዓፀር፤

በመከራ፡ በዓፀር፡ ተይዛችሁ፡ ሳለ፡ ከናንተ፡ ወገን፡ ማርከው፡ ይወስዳሉ፤

፲፪፤ እምይእዜሰ፡ አልብኪ፡ ሠናይት፤

እንግዲህስ፡ ወዲህ፡ ተድላ፡ ደስታ፡ የለሽም፤

ንበሪ፡ ሕምምተኪ፤

በመከራ፡ ተይዘሽ፡ ኑሪ፤

እስመ፡ ወረደት፡ እኪት፡ እምኀበ፡ እግ ዚአብሔር፡ ላዕለ፡ አናቅጸ፡ ኢየሩሳሌም፤

በኢየሩሳሌም፡ ባሉ፡ ሰዎች፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ መከራ፡ ታዝዛለችና፤



፲፫፤ ድምፀ፡ ሠረገላ፡ ወአፍራስ፡ ላዕለ፡ እንተ፡ ትነብር፡ ለኪሶ፤

ይሰማዕ፡ ያለበት፡ ነው፤ በለ ኪሶ፡ በምትኖር፡ በቤተ፡ እስራ ኤል፡ የፈረስ፡ የሠረገላ፡ ድምፅ፡ ይሰማል፤

መልአከ፡ ኃጢአታ፡ ይእቲ፡ ለወለተ፡ ጽዮን፤

የጽዮን፡ ልጅ፡ የኃጢአቷ፡ መል ክተኛ፡ ይች፡ ናት፤ የለኪሶ፡ ሰዎች፡ ዐሥሩን፡ ነገድ፡ ይገ ዛሉ፤ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ለለኪሶ፡ ሰዎች፡ ይገዛሉና፤ አንድም ሁለቱ፡ ነገድ፡ የለኪሶንን፡ ሰዎች፡ ጌሻ፡ አድርገው፡ ጌት፡ ከሚባል፡ አገር፡ ይገዛሉና፤

እስመ፡ በላዕሌኪ፡ ተረክበ፡ ጣዖተ፡ እስራኤል፡ በእንተ፡ ዘፈነውኪ፡ ሐዋር ያተ፡ ውስተ፡ ጌት፤

ወደ፡ ጌት፡ መልክተኛ፡ ስለ፡ ሰደድሽ፡ የእስራኤል፡ ጣዖት፡ በአንቺ ዘንድ፡ ተገኝቷልና፤

፲፬፤ ከንቶ፡ ኮኑ፤

እነዚህም፡ ከንቱ፡ ሆኑ፤

ወአርቁ፡ አብያተ፡ መንግሥተ፡ እስራኤል፤

የእስራኤል፡ የነገሥታቱ፡ ቤቶች፡ ገንዘቡ፡ ተማርኮ፡ ሄዶ፡ በደዋቸውን፡ ሆኑ፤

፲፭፤ ወይወስድዎሙ፡ ለሰብአ፡ ለኪሶ፡ ኀበ፡ መዋርስት፡ እስከ፡ ኤላም፤

የለኪሶን፡ ሰዎች፡ ወርሰዋቸው፡ ወደሚኖሩ፡ ወደባቢሎን፤ ወደ ፋርስ፡ ይወስዷቸዋል፤

ወያመጽኡ፡ ክብራ፡ ለወለተ፡ ጽዮን፤

የጽዮንን፡ ልጅ፡ ባለጸግነቷን፡ ማርከው፡ ወደባቢሎን፡ ያመ ጣሉ፤ ነቢዩ፡ በባቢሎን፡ እን ዳለ፡ ሆኖ፡ ያመጽኡ፡ አለ፤

ወያመጽእዎሙ፡ ዬዋ፡ እን ዲል፤ አንድም፡ ይወስዱ፡ ሲል፡ ነው፤ ማርከው፡ ይወስዱታል፤

ገየምዒ፡ ርእሰኪ፤

ራስሽን፡ (ፀጉርሺን)፡ ቍረጪ፤

ወተላፀዪ፡ ላዕለ፡ ደቂቅኪ፡ ልህድ፡

ድልድል፡ ቅምጥል፡ የምትሆኝ፡ ጽዮን፡ ለልጆችሽ፡ ጠጕርሽን፡ ተላጪ፤

አርኀቢ፡ ብርሀተኪ፡ ከመ፡ ንስር፤

ትብትብ፡ ምንጣፍ፡ በመሸከም፡ ራስሽ፡ እንደቁራ፡ ቡሃ፡ ይሁን፤

እስመ፡ ፄወውዎሙ፡ እምኀቤኪ፤

ካንቺ፡ ዘንድ፡ ማርከው፡ ወስደ ዋቸዋልና።

www.ethiopianorthodox.org

ወአኅደግዎ፡ ትውክልቶ፤

የሚታመንበትን፡ ጋሻውን፡ ጦሩን፡ አስጣሉት፤

ወይቀጠቅጥዎ፡ በውስተ፡ ቀትል፤

በሰልፍ፡ መካከል፡ ይገድሉታል፤

፱፤ ወበበይነ፡ ዝንቱ፡ ይገድፍዎሙ፡ ለመላእክቲ፡ ሕዝብየ፡ እምውስተ፡ ትርሢተ፡ አብያቲሆሙ፤

እምውስተ፡ ርሡይ፡ ሲል፡ ነው፤ ስለዚህ፡ ነገር፡ ከተነጠፈ፡ ከተጋረደ፡ ቤታቸው፡ የወገኖቼን፡ አለቆች፡ እየወጉ፡ ይጥሏቸዋል፤

ወይወስድዎሙ፡ እስመ፡ እኩይ፡ ምግባሪሆሙ፤

ግብራቸው፡ ክፉ፡ ነውና፡ ማርከው፡ ይወስዷቸዋል፤

ቅረቡ፡ አድባር፡ እለ፡ እምፍጥረተ፡ ዓለም፤

ከጥንት፡ ጀምሮ፡ የነበራችሁ፡ የአሕዛብ፡ ነገሥታት፡ እስራኤልን፡ ለመማረክ፡ ቅረቡ፤ አንድም፡ የእስራኤል ነገሥታት፡ አሕዛብን፡ ለመማረክ፡ ቅረቡ፤

፲፤ ተንሥኡ፡ ወሑሩ፤

የአሕዛብ፡ ነገሥታት፡ እስራኤልን፡ ለመማረክ፡ ተነሥታችሁ፡ ሂዱ፤ አንድም፡ የእስራኤል፡ ነገሥታት፡ ተማርከ፡ ለመሄድ፡ ተነሡ፤

እስመ፡ ኢኮነት፡ እንተ፡ አክሙ፡ ዛቲ፡ ዕረፍት፡ ይእቲ፤

ይህቺ፡ እረፍት፡ ለናንተ፡ የምትገባችሁ፡ አይደለምና፤

በእንተ፡ ርኵስክሙ፡ ጠፋእክሙ፡ ወኃለቅሙ፤

ኃጢአት፡ ስለሠራችሁ፤ አንድም፡ ጣዖት፡ ስላመለካችሁ፡ ፈጽማችሁ፡ ጠፋችሁ፤

፲፩፤ ወጉየይክሙ፡ እንዘ፡ አልቦ፡ ዘይዴግነክሙ፤

የሚከተላችሁ፡ ሳይኖር፡ ሸሻችሁ፤

ጋኔን፡ ዓቀመ፡ ለከ፡ ሐሰተ፤

ጋኔን፡ ጣዖት፡ እንድታመልክ፡ አደረገህ፤ አንድም፡ ጋኔን፡ ኢዮርብአም፡ ጣዖት፡ አቆመልህ፤

ወአውጻሕከ፡ ሎቱ፡ ወይነ፡ ወጼተሎ፤

የወይን፡ ጠጅ፤ የማር፡ ጠጅ፡ አፈሰስህለት፤ ትርጓሜው፡ እንዳለፈው፡ ነው፤

ወይከውን፡ በነፍነፎሙ፡ ለዝንቱ፡ ሕዝብ፤

በተረፎሙ፡ ሲል፡ ነው፤ ዐሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ በቀሩ፡ በሁለቱ፡ ነገድ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤



፲፪፤ ወይትጋባዕ፡ ያዕቆብ፡ ምስለ፡ ኵሎሙ፡ እለ፡ ይጸንሑ፡ እምጽንሖሙ፡ ለተረፈ፡ እስራኤል፤

ዐሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀሩ፡ የሁለቱን፡ ነገድ፡ አለኝታ ደጅ፡ ከሚጠኑ፡ ካሥሩ፡ ነገድ፡ ጋራ፡ ያዕቆብ፡ አንድ፡ ይሆናል፤

ወእሬስዮ፡ ኅቡረ፡ ለሚጠቶሙ፤

መመለሳቸውን፡ አንድ፡ አደርጋታለሁ፤

ከመ፡ አባግዕ፡ ውስተ፡ መፅብብ፤

በግ፡ ወደ፡ ጠባብ፡ ቦታ፡ እንዲገባ፤

ወከመ፡ መርዔት፡ ውስተ፡ ምብያቲሁ፤

መንጋውም፡ ወደ፡ ቤቱ፡ እንዲገባ፡ አንድ፡ ሁነው፡ ወደ፡ ኢየሩሳሌም፡ ይመለሳሉ፤

ወይትባልሑ፡ እምሰብእ፡ እኩያን፤

ከክፉ፡ ሰዎች፡ ይድናሉ፤

፲፫፤ በእንተ፡ ቅትለቶሙ፡ ዘተቀትሉ፡ በቅድመ፡ ገጾሙ፤

ሰባ፡ ዘመን፡ በፊታቸው፡ መከራ፡ ስለተቀበሉ፤

ወኃለፉ፡ እምአንቀጽ፡ ወወጽኡ፡ እንተ፡ ውስቴታ፤

በባቢሎን፡ አደባባይ፡ እየተዋጉ፡ ወጡ፤

ወሖረ፡ ንጉሦሙ፡ በቅድሜሆሙ፤

ንጉሣቸው፡ ዘሩባቤል፡ በፊታቸው፡ ጉምስል፡ ጉምስል፡ እያለ፡ ሄደ፤

ወእግዚአብሔር፡ ይመርሆሙ፤

እግዚአብሔር፡ ይመራቸው፡ ነበርና።

## ምዕራፍ ፫

፩፤ ወይብል፡ ስምዑ፡ ዘንተ፡ መኳንንተ፡ ቤተ፡ ያዕቆብ፤

የያዕቆብ፡ ወገኖች፡ መኳንንቱ፡ ስሙ፤

ወተረፈ፡ ቤተ፡ እስራኤል፤

ዐሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀራችሁ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ስሙ፤

ኢኮነ፡ ለክሙ፡ አእምሮ፡ ጥበብ፡ ወፍትሕ፡ እለ፡ ትጸልዑ፡ ሠናየ፡ ወተኃሥሡ፡ እኩየ፤

ክፉውን፡ ነገር፡ የምትፈልጉ፡ በጎውን፡ ነገር፡ የምትጠሉ፡ ጥበብን፡ ማወቅ፡ እውነት፡ ፍርድን፡ መፍረድ፡ አልተቻላችሁም፤

፪፤ ወትመሥጥዎሙ፡ አምእስቲሆሙ፡ እምላዕሌሆሙ፡ ወሥጋሆሙኒ፡ እምውስተ፡ አዕፅምቲሆሙ፤

ቁርበታቸውን፡ ከሥጋቸው፤ ሥጋቸውን፡ ከአጥንታቸው፡

www.ethiopianorthodox.org

ለይታችሁ፡ ትበላላችሁ፡ ማለት፡ ገንዘባቸውን፡ ከሳቸው፡ ለይታ ችሁ፡ ትወስዱታላችሁ፤

፫፤ ወበከመ፡ በልዑ፡ ሥጋሆሙ፡ ለሕዝብየ፡ ወአውጽኡ፡ አምእስቲሆሙ፡ እምላዕለ፡ አዕፅምቲሆሙ፤

የወገኖቼን፡ ገንዘባቸውን፡ በበሉ፡ ጊዜ፤

ወገመዱ፡ መሌሊቶሙ፤

ሰውነታቸውን፡ በቆረጡ፡ ጊዜ፡ ማለት፡ በውስጥ፡ በአፍአ፡ ያለ፡ ገንዘባቸውን፡ ባጠፉ፡ ጊዜ፤

ከመ፡ ሥጋ፡ ውስተ፡ ጽሕርት፡ ወከመ፡ አባል፡ እምውስተ፡ መቅጹት፡ ቀዲሙ፤

በሳመፌጅ፡ ድስት፡ እንዳለ፡ ሥጋ፡ ይሆናሉ፤ ያ፡ ባዩት፡ ጊዜ፡ መሸከ፡ እንዲገኝ፤

፬፤ ቀዲሙ፡ ከማሁ፡ ይጸርሑ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ወኢይሰምዖሙ፤

ጽኑ፡ መከራ፡ መጥቶባቸው፡ ከእግዚአብሔር፡ ዘንድ፡ ይለ ምናሉ፤ ልመናቸውንም፡ አይ ሰማቸውም፤

ወይመይጥ፡ ገጾ፡ እምኔሆሙ፡ ይእተ፡ አሚረ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ፊቱን፤ አንድም፡ ገጸ፡ ረድኤቱን፡ ከሳቸው፡ ይመልሳል፤

እስመ፡ አሕሰሙ፡ ገቢረ፡ በላዕሌሆሙ፤

በላያቸው፡ ላይ፡ ክፉ፡ ነገር፡ አድርገዋልና፤

፭፤ ከመዝ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፡ ላዕለ፡ ነቢያት፡ እለ፡ ያስሕትዎሙ፡ ለሕዝብየ፤

ወገኖቼን፡ በሚያስቱ፡ በነቢያተ፡ ሐሰት፡ በመዓት፡ አለሁባቸው፤

ወእለ፡ ይኔዝርዎሙ፡ በስነኒሆሙ፤

በጥርሳቸው፡ የሚበታትኗ ቸው፡ ማለት፡ በትምህርት፡ በሚለያዩዋቸው፡ በመዓት፡ አለሁባቸው፤

ወይሰብኩ፡ ሎሙ፡ ሰላመ፡ ዘአልቦ፡ ዘአዘዞሙ፤

ያዘዛቸው፡ ሳይኖር፡ አይዟችሁ፡ ዜዋዌ፡ የለም፡ እያሉ፡ የሚ ያስተምሩ፤

ወአንሥኡ፡ ላዕሌሆሙ፡ ቀትለ፤

በርሳቸው፡ ላይ፡ ሰልፍም፡ በአ መጡባቸው፡ በመዓት፡ አለ ሁባቸው፤

፮፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ሌሊተ፡ ይከውነክሙ፡ ራእይክሙ፡ ጽልመተ፡ ይከውነክሙ፡ ሰገልክሙ፤

ራእይክሙ፡ ሰገልክሙ፡ አንድ፡ ወገን፤ ሌሊት፡ ጽልመት፡



አንድ፡ ወገን፤ ራእይ፡ ዓየን፡ የምትሉት፡ የምትጠነቁሉት፡ ጥንቆላ፡ ሐሰት፡ ይሆንባችኋል፤

ወየዓርቦሙ፡ ፀሐይ፡ ለነቢያት፡ ወይ ጸልሞሙ፡ መዓልት፤

የዓርቦሙ፡ ወይጸልሞሙ፡ አንድ፡ ወገን፤ የነቢያተ፡ ሐሰት፡ ትንቢታቸው፡ ሐሰት፡ ይሆን ባቸዋል፤

፯፤ ወይትሐፈሩ፡ ሐሳምያን፡ ሕልመ፡ ሐሰት፤

ሐሰተኛውን፡ ሕልም፡ አለምነ፡ የሚሉ፡ ያፍራሉ፤

ወይስሕቅዎሙ፡ ለሰብእ፡ ሰገል፡ ወይ ኄምይዎሙ፡ ለኵሎሙ፤

ጥንቆላ፡ ያላቸውን፡ ሰዎች፡ መከራ፡ ያጸኑባቸዋል፤ አሥረው፡ ያግዟቸዋል፤

ወአልቦ፡ ዘያጸምዖሙ፡ እንከ፤

እንግዲህ፡ ወዲህ፡ የሚሰማ ቸው፡ የለም፤

፰፤ ለእመ፡ ኢመላዕኩ፡ ኀይለ፡ መን ፈስ፡ እግዚአብሔር፡ ኀይለ፡ ወፍትሐ፤

እውቀትን፡ ፍርድን፡ የሚገልጥ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ ባላሳድርባ ቸው፡ ሐሰት፡ ተናግረው፡ የሚሰ ማቸው፡ የለም፤ አንድም፡ እው ቀትን፡ ፍርድን፡ የሚገልጽ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ እኔ፡ ካላሳ ደርሁባቸው፡ ማን፡ ያውቃል?

ከመ፡ ይንግሩ፡ ኃጢአቶ፡ ለያዕቆብ፤

የያዕቆብን፡ ኃጢአቱን፡ ይነግሩ፡ ዘንድ፤

ወለእስራኤል፡ ጌጋዮ፤

የእስራኤልንም፡ በደሉን፡ ይነ ግሩ፡ ዘንድ፤

፱፤ ስምዑ፡ ዘንተ፡ መኳንንተ፡ ቤተ፡ ያዕቆብ፤

የያዕቆብ፤ ወገን፡ መኳንንቱ፡ ስሙ፤

ወተረፈ፤ ቤተ፡ እስራኤል፤

አሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀ ራችሁ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ስሙ፤

እለ፡ ታስቈርርዋ፡ ለጽድቅ፡ ወትገፈ ትዕዋ፡ ለርትዕ፤

እውነተኛ፡ ሕግን፡ የምትጠ ሏት፡ የቀናች፡ ሕግን፡ ጠማማ፡ የምታደርጓት፤

፲፤ እለ፡ ተሐንፅዋ፡ ለጽዮን፡ በደም፤

የሰውን፡ ደም፡ በማፍሰስ፡ ጽዮ ንን፡ የምትሠሯት፤ አንድም፡ የድኃውን፡ ገንዘብ፡ በመቀማት፡ የምትሠሯት፤

www.ethiopianorthodox.org

ወለኢየሩሳሌምኒ፡ በዓመፃ፤

ኢየሩሳሌምን፡ በግፍ፡ የምት ሠሯት፡ ስሙ፤

፲፩፤ መኳንንቲሃኒ፡ በሕልያን፡ ይኴንኑ፤

መኳንንቱ፡ መማለጃ፡ ተቀብ ለው፡ ይፈርዳሉ፤

ወካህናቲሃኒ፡ በዓስብ፡ ያወሥዑ፤

ካህናቱም፡ ዋጋ፡ ተቀብለው፡ ያስተምራሉ፤

ወነቢያቲሃኒ፡ በወርቅ፡ ያሰግሉ፤

ነቢያቶችዋም፡ ወርቅ፡ ተቀብ ለው፡ ይጠነቍላሉ፤

ወላዕለ፡ እግዚአብሔር፡ ያሰምኩ፤

እንዲህ፡ እያደረጉ፡ እግዚአብ ሔር፡ አድሮብናል፡ በእግዚአ ብሔር፡ አመንን፡ ይላሉ፤

ወይብሉ፡ አኮኑ፡ እግዚአብሔር፡ ምስ ሌነ፡ ወኢይረክበነ፡ እኩይ፤

እግዚአብሔር፡ ከኛ፡ ጋር፡ ያለ፡ አይደለምን፡ መከራ፡ አያገኘ ንም፡ ይላሉ፤

፲፪፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ በበይነ፡ ዚአ ክሙ፡ የሐርስዋ፡ ለጽዮን፡ ከመ፡ ገራህት፤

በእንተ፡ ዝንቱና፡ በበይነ፡ ዚአ ክሙ፡ አንድ፡ ወገን፤ ስለዚህ፡ ነገር፡ በናንተ፡ ኃጢአት፡ ምክ ንያት፡ ጽዮንን፡ እንደ እርሻ፡ ያርሷታል፤ ጎንደር፡ ይታረስ፡ እንዲሉ፤ አንድም፡ በዳዊት፤ በሰሎሞን፡ መቃብር፡ ወርቅ፡ እንደተገኘ፡ ወርቅ፡ እናገኛለን፡ ብለው፤

ወትከውን፡ ኢየሩሳሌም፡ ከመ፡ ልገተ፡ ዓቃቤ፡ ቀምሕ፤

ኢየሩሳሌም፡ እንደፍሬ፡ ጠባቂ፡ ጎጆ፡ ትሆናለች፤

ወደብረ፡ ቤቱሂ፡ ከመ፡ ዖመ፡ ገዳም፤

አምስቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፡ ስድ ስቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፡ ሰባቱ፡ ቆመ፡ ብእሲ፡ ምድረ፡ በዳ፡ ይሆናል።

## ምዕራፍ ፬

፩፤ ወይከውን፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፤

በሕዝቅያስ፡ ዘመን፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤

ያስተርኢ፡ ቤተ፡ እግዚአብሔር፡ ድልው፡ ውስተ፡ አርእስተ፡ አድባር፡ ወይትሌዓል፡ መልዕልተ፡ አውግር፤

ይከውን፡ ያለውን፡ ያስተርኢ፡ ብሎ፡ አመጣው፤ በሕዝቅያስ፡ ጊዜ፡ ቤተ፡ መቅደስ፤ በኪዳነ፡ አብርሃም፤ በኪዳነ፡ ይስሐቅ፤ በኪዳነ፡ ያዕቆብ፡ ጸንቶ፡



ይታያል፤ በዘሩባቤል፡ ጊዜ፡ ቢሉ፡ ባምስቱ፤ በስድስቱ፤ በሰባቱ ቆመ፡ ብእሲ፡ ጸንቶ፡ ይታያል፤

፪፤ ወየሐውሩ፡ ብዙኃን፡ አሕዛብ፤

ብዙ፡ አሕዛብ፡ ወደ፡ ቤተ፡ መቅ ደስ፡ ይሄዳሉ፤

ወይብሉ፡ ንዑ፡ ንዕርግ፡ ውስተ፡ ደብረ፡ እግዚአብሔር፤

ከመሄዳቸው፡ አስቀድመው፡ ኑ፡ ወደቤተ፡ እግዚአብሔር፡ እን ሒድ፡ ይላሉ፤

ወውስተ፡ ቤተ፡ አምላኩ፡ ያዕቆብ፤

ወደያዕቆብ፡ ፈጣሪ፡ ማደሪያ፡ ወደቤተ፡ መቅደስ፡ እንሂድ፡ ይላሉ፤

ይንግሩነ፡ ፍኖቶ፡ ወንሑር፡ በዓሠሩ፤

ዘጠኙን፡ ቃላት፡ ያስተምሩን፡ ዘንድ፡ በኢታምልክም፡ ጸንተን፡ እንኖር፡ ዘንድ፡ ኢታምልክን፡ ዐሠር፡ አላት፤ ፍለጋ፡ ከሀገር፡ ከመንደር፡ እንዲያደርስ፡ ኢታ ምልክም፡ ከዘጠኙ፡ ቃላት፡ ታደ ርሳለችና፤ ይንግሩነ፡ ፍኖቶ፡ ወዓሠሮ፤ ኢታምልክን፡ ዘጠኙን፡ ቃላት፡ ይነግሩን፡ ዘንድ፤ አን ድም፡ ንሑር፡ በዓሠሩ፡ ወበፍ ኖቱ፡ ይላል፤ በኢታምልክ፡ በዘ ጠኙ፡ ቃላት፡ ጸንተን፡ እንኖር፡ ዘንድ፤

እስመ፡ እምጽዮን፡ ይወጽእ፡ ሕግ፡ ወቃለ፡ እግዚአብሔር፡ እምኢየሩሳሌም፤

ከነቢያት፡ ትንቢት፡ ከካህናት፡ ትምህርት፡ ይገኛልና፤ አንድም፡ ከነቢያት፡ ትንቢት፤ ከካህናት፡ ትምህርት፡ ይገኛልና፤ ኑ፡ ወደቤተ፡ እግዚአብሔር፡ እን ሂድ፡ ይላሉ፡ ይላል፡ ነቢዩ፤ አንድም፡ ወይከውን፡ በደኃሪ፡ መዋዕል፡ ብለህ፡ መልስ፤ በዘመነ፡ ሐዲስ፡ በጌታ፡ ጊዜ፡ እንዲህ፡ ይሆናል፤ በወርቅ፡ በብር፡ ከተሠራ፡ ከነገሥታቱ፡ ቤት፡ በኖራ፡ በጭቃ፡ የተሠራ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ በማዕርግ፡ በልጦ፡ ይታያል፤ ወደቤተ፡ ክርስቲያን፡ ከመሄዳቸው፡ አስ ቀድሞ፡ ኑ፡ ወደቤተ፡ ክርስቲ ያን፡ እንሂድ፡ ይላሉ፤ ዘጠኙን፡ ቃላት፡ ኢታምልክን፡ ይነግሩን፡ ዘንድ፤ በሕገ፡ ወንጌልም፡ ጸን ተን፡ እንኖር፡ ዘንድ፡ ሕግ፡ ጌታ፡ ከእመቤታችን፡ ይወለዳ

www.ethiopianorthodox.org

ልና። አንሶሰወት፡ ሕግ፡ ወአስተርአየት፡ ውስተ፡ ዓለም እንዲል፤ አንድም፡ ሐጋጊ፡ ሕግ፡ ጌታ፡ ከእመቤታችን፡ ተወልዷልና፡ ጽዮን፡ አላት። ፀወነ፡ ሥጋ። ፀወነ፡ ነፍስ፡ ናትና። አካላዊ፡ ቃል፡ እርሱ፡ ከእመቤታችን፡ ተወልዷልና። ኢየሩሳሌም፡ እንጂ፡ ማለት፡ መካነ፡ ሰላም፡ ማለት፡ ነው። እሷንም፡ ብኪ፡ ድኅነ፡ ዓለም፡ ወበወልድኪ፡ ኮነ፡ ሰላም፡ ይላታልና፤ አንድም፡ ሕግ፡ ወንጌል፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ይነገራልና። አካላዊ፡ ቃል፡ እርሱ፡ በሥጋነት፡ በደምነት፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡ ይገኛልና፡ ወደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ እንሂድ፡ ይላሉ፤

፫፤ ወይኬንን፡ በማዕከለ፡ አሕዛብ።

ዘሩባቤል፡ በአሕዛብ፡ መካከል፡ ይፈርዳል፤

ወይዛለፎሙ፡ ለአሕዛብ፡ ጽኑዓን፡ እስከ፡ ነዋኃት፡ አድባር፡ ወብሔር።

ጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ ያሉ፡ ጽኑዓን፡ አሕዛብን፡ ብትገብሩ፡ ገብሩ፡ ያለዚያ፡ እወጋችኋለሁ፡ እያለ፡ ይዘልፋቸዋል፤

ወይመትሩ፡ ኵያንዊሆሙ፡ ለምሳር።

ጦራቸውን፡ ምሳር፡ አድርገው፡ ይጨፈልቁታል።

ወአስይፍቲሆሙ፡ ለማዕፀድ።

ሰይፋቸውን፡ ማጭድ፡ አድርገው፡ ያሠሩታል፤

ወኢያነሥኡ፡ እንከ፡ ሕዝብ፡ ዲበ፡ ሕዝብ፡ መጥባሕተ።

አንዱ፡ በአንዱ፡ ላይ፡ ጦር፡ አያነሣም፡ ዘመኑ፡ ዘመነ፡ ሰላም፡ ሆኖ፤ ይበልዑ፡ ወይሰትዩ፡ ታሕተ፡ ወይኖሙ፡ ወበለሶሙ፡ ወይነብሩ፡ ተአሚኖሙ፡ እንዲል። ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ አርፈው፡ ይኖራሉ፤

ወኢይትሜሀሩ፡ እንከ፡ ቀትለ።

ሰልፍ፡ አይማሩም። ሰልፍ፡ መማር፡ አለና። በፈረስ፡ እየጋለቡ፡ የአንዱን፡ እግር፡ ሰናፊል፡ በአንድ፡ እግር፡ ማግባት። በአረቂ፡ መርፌ፡ ፈትል፡ ማግባት። ዘንግ፡ ወርውሮ፡ መቅለም። አለንጋ፡ ማንሳት፡ አለና፤ አንድም፡ ወይኬንን፡ ማዕከለ፡ አሕዛብ፡ ብለህ፡ መልስ። ጌታ፡ በአሕዛብ፡ መካከል፡ ተሐድገ፡ ለኪ፡ ኃጢአትኪ፡ ፈቀድኩ፡ ንጻሕ። ተንሥእ፡ ንሣእ፡ አራተከ፡ እያለ፡



ይፈርዳል። ጸሐፍት፡ ፈሪሳውያንን፡ አሌ፡ ለክሙ፡ ጸሐፍት፡ ፈሪሳውያን፡ መደልዋን፡ እያለ፡ ይዘልፋቸዋል። ጦራቸውን፡ መቆፈሪያ፡ አድርገው፡ ያሠሩታል። ሰይፋቸውንም፡ ሠቅ፡ መስቀል፡ አድርገው፡ ያሠሩታል። አንዱ፡ በአንዱ፡ ላይ፡ ጠብ፡ አያነሳም። ዘመኑ፡ ዘመነ፡ ሰላም፡ ሆኖ። ወያጠፍዕ፡ ሠረገላ፡ እምኤፍሬም፡ ወአፍራሰ፡ እምይሁዳ፡ ወይከውን፡ ሰላም፡ በመዋዕሊሁ፡ እንዲል፡ ሰልፍ፡ አይማሩም። ሐተታው፡ እንዳለፈው፡ ነው፤

፬፤ ወየአርፉ፡ ኵሎሙ፡ ታሕተ፡ ወይኖሙ፡ ወበለሶሙ።

ከወይኑ፡ ከበለሱ፡ ሥር፡ አርፈው፡ ይኖራሉ፤

ወአልቦ፡ ዘይጌርሞሙ።

የሚያስፈራቸው፡ የለም፤

እስመ፡ አፉሁ፡ ለእግዚአብሔር፡ ዘኵሎ፡ ይመልክ፡ ነበበ፡ ከመዝ።

ሁሉን፡ የሚገዛ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ተናግሯልና፤

፭፤ እስመ፡ ኵሎሙ፡ አሕዛብ፡ የሐውሩ፡ በፍናቶሙ።

አሕዛብ፡ በኃጢአታቸው፡ ጸንተው፡ የሚኖሩ፡ ስለሆኑ።

ወንሕነሰ፡ ንሐውር፡ በስመ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክነ፡ ለዓለመ፡ ዓለም።

እኛ፡ ግን፡ ለዘለዓለሙ፡ በእግዚአብሔር፡ አምነን፡ እንኖራለን፤

፮፤ ወዓዲ፡ ይእቲ፡ አሚረ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር።

ዳግመኛ፡ ያን፡ ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አለ፤

አስተጋብኣ፡ ለዝሩት።

ሁለቱን፡ ነገድ፡ እሰበስባቸዋለሁ።

ወእትዌከፋ፡ ለግድፍት፡ ለእንተ፡ አርኃቅዋ።

ብዙ፡ ዘመን፡ ያራቅኋት። በመከራ፡ የጣልኋት፡ ዐሥሩን፡ ነገድ፡ በረድኤት፡ እቀበላታለሁ። እንዲህ፡ ስላለ፡ ግን፡ በግድፍት፡ ዝሩት። በዝሩት፡ ግድፍት፡ ያለበት፡ ነው፤

፯፤ ወእሬስያ፡ ለዝሩት፡ ትርፍተ። ወለግድፍት፡ ሕዝበ፡ ጽንዕተ።

ሁለቱን፡ ነገድ፡ ብዙ፡ አደርጋታለሁ። በመከራ፡ የጣልኋት፡ አሥሩን፡ ነገድ፡ አጸናታለሁ፤

ወይነግሥ ሎሙ፡ እግዚአብሔር፡ በደብረ፡ ጽዮን፡ እምይእዜ፡ ወእስከ፡ ለዓለም።

ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ እግዚአብሔር፡ ለዘላለሙ፡ በደብረ፡ ጽዮን፡

www.ethiopianorthodox.org

ነግሦላቸው፡ ይኖራል፤ አንድም፡ በማኅፀነ፡ ማርያም፡ የባሕርይ፡ መንግሥት፡ ይነግሥላቸዋል፤ አንድም፡ በቀራንዮ፡ በመስቀል፡ በደብረ፡ ጽዮን፡ ይነግሥላቸዋል፤

፰፤ ወአንቲኒ፡ ማኅፈደ፡ ኖሎት፡ ከመ፡ ፀበል፡ ትከውኒ፤

አንቺም፡ የዳዊት፡ የሰሎሞን፡ ከተማ፡ ቤተልሔም፡ እንደት ቢያ፡ ትሆኛለሽ፤

ወትመጽእ፡ ወለተ፡ ባቢሎን፡ ውስቴትኪ፤

የባቢሎን፡ ልጅ፡ ወደአንቺ፡ ትመጣለች፤

ወትቀድም፡ መዊዓ፡ ቀዳሚተ፡ መንግሥት፡ ወለተ፡ ባቢሎን፡ እምወለተ፡ ኢየሩሳሌም፤

በመንግሥት፡ የምትቀድም፡ የባቢሎን፡ ልጅ፡ ከኢየሩሳሌም፡ ልጅ፡ አስቀድማ፡ ድል፡ ትነሣለች፤ አንድም፡ ወትቀድም፡ መዊዓ፡ ወለተ፡ ኢየሩሳሌም፡ እምወለተ፡ ባቢሎን፡ ቀዳሚተ፡ መንግሥት፡ ሲል ነው፤ የኢየሩሳሌም፡ ልጅ፡ በመንግሥት፡ ከምትቀድም፡ ከባቢሎን፡ ልጅ፡ አስቀድማ፡ ድል፡ ትነሣለች፤

፱፤ ወይእዜኒ፡ ለምንት፡ መከርኪ፡ እኩየ፤

አሁንስ፡ ለምን፡ እንዲህ፡ ብለሽ፡ መከርሽ፤

ንጉሥኑ፡ አልብኪ፤

የሚሠራ፡ የሚቀጣ፡ ንጉሥ፡ የለሽም?

ጠፍአኑ፡ ልብኪ፤

አእምሮሽ፡ ጠፋን፤

ከመ፡ የአኃዝኪ፡ ማሕምም፡ ከመ፡ እንተ፡ ትወልድ፤

እንደምትወልድ፡ ሴት፡ ምጥ፡ ይይዝሽ፡ ዘንድ፤

፲፤ ሐመምኪዪ፡ ወተዕዕርኪ፡ ወተአገሥኪ፡ እንከ፡ ወለተ፡ ጽዮን፡ ከመ፡ እንተ፡ ትወልድ፤

የጽዮን፡ ልጅ፡ እንደምትወልድ፡ ሴት፡ በመከራው፡ ተይዘሽ፡ ተጨነቅሽ፤ መከራውን፡ ታገሥሽ፤

እስመ፡ ናሁ፡ ይእዜ፡ ትወጽኢ፡ እምሀገር፡ ወተኃድሪ፡ ውስተ፡ ገዳም፤

እነሆ፡ ዛሬ፡ ከሀገርሽ፡ ወጥተሽ፡ ትሄጃለሽና፡ በምድረ፡ በዳው፡ ታድሪያለሽ፤ ብዛታቸውን፡ መናገር፡ ነው፤

ወትበጽሒ፡ እስከ፡ ባቢሎን፡

እስከ፡ ባቢሎን፡ ድረስ፡ ትሄጃለሽ



ወበህየ፡ ያድኅነኪ፡ ወያነግፈኪ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክኪ፡ እምእደ፡ ፀርኪ፤

ፈጣሪሽ፡ እግዚአብሔር፡ ከጠላቶችሽ፡ እጅ፡ ያድንሻል፤

፲፩፤ ወናሁ፡ ይእዜ፡ ይትጋብዑ፡ ብዙኃን፡ አሕዛብ፡ ላዕሌኪ፡ እለ፡ ይብሉ፤

ንትፌሣሕ፡ ላዕሌኪ፡ ብኪ፡ ሲል፡ ነው፤ ብዙ፡ አሕዛብ፡ ባንቺ፡ ጥፋት፡ ደስ፡ ይበለን፡ የሚሉ፡ ይሰበሰባሉ፤

ወይሬእያ፡ አዕይንቲነ፡ ጽዮን፤

ጽዮን፡ ያንቺን፡ ጥፋት፡ ዓይኖቻችን፡ ይዩ፡ የሚሉ፡ አሕዛብ፡ በአንቺ፡ ላይ፡ ይሰበሰባሉ፤

፲፪፤ ወእሙንቱሰ፡ ኢያእመሩ፡ ዘመከረ፡ እግዚአብሔር፤

እነሱ፡ ግን፡ ፳ኤል፡ ይዳኑ፤ አሕዛብ፡ ይጥፉ፡ ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ የመከረውን፡ አላወቁም፤

ወኢያእመሩ፡ ዘሐለየ፤

ያሰበውንም፡ አላወቁም፤

ወቅረቢ፡ ለመከራ፤

መከራ፡ ለመቀበል፡ ቅረቢ፤

እስመ፡ አስተጋብኦሙ፡ ከመ፡ ከላስስት፡ ውስተ፡ ዓውደ፡ እክል፤

እንደ፡ ነዶ፡ በዓውድማ፡ እሰበስባቸዋለሁና፤

፲፫፤ ተንሥኢ፡ አኪዲዮሙ፡ ወለተ፡ ጽዮን፤

ተነስተሽ፡ አበራዪያቸው፤

እስመ፡ እሬስዮ፡ ዘሐዲን፡ ለሠረገላኪ፤

ሠረገላሽን፡ የብረት፡ አደርገዋለሁና፤

ወእሬስዮ፡ ዘብርት፡ ለመንኰራኵርኪ፤

መንኰራኵርሽንም፡ የብርት፡ አደርገዋለሁና፡ ማለት፡ ሥልጣንሽን፡ አጠናዋለሁ፤

ወትመመውዒዮሙ፡ ለብዙኃን፡ አሕዛብ፤

ብዙ፡ አሕዛብንም፡ ድል፡ ትነሻቸዋለሽ፤

ወተኃርሚዮሙ፡ ለእግዚአብሔር፡ በዙሉ፡ ምድር፤

ለእግዚአብሔር፡ ብለሽ፡ በዓለሙ፡ ሁሉ፡ ሥርዓተ፡ ሞት፡ ትሠሪባቸዋለሽ፤ አንድም፡ ከሕይወት፡ እርም፡ ታደርጊያቸዋለሽ፡፡

## ምዕራፍ ፭

፩፤ ናሁ፡ ይእዜ፡ የዓግትዋ፡ ለወለተ፡ ጽዮን፡ ወየኃዕርዋ፤

የጽዮንን፡ ልጅ፡ በጦር፡ ይከብቧታል፡ በጦር፡ ያጥሯታል፤

ወበበትር፡ ይዘብጡክሙ፡ መላትሒክሙ፡ ሕዝበ፡ እስራኤል፤

የእስራኤል፡ ወገኖች፡ ፊታችሁን፡ በአኮርባጅ፡ እየመቱ፡ ይወስዷችኋል፤

www.ethiopianorthodox.org

## ጉባዔ

፪፤ ወአንቲኒ፡ ቤተልሔም፡ ምድረ፡ ኤፍራታ፡ ውኅድ፡ አንቲ፡ ከመ፡ ትኩኒ፡ ውስተ፡ አዕላፈ፡ ይሁዳ፤

አንችም፡ ቤተልሔም፡ ኊላ፡ ትበገር፡ ዘንድ፡ ዛሬ፡ አንሰ ሻል፤ አንድም፡ ዛሬ፡ አንሰሽ፡ ያለ፡ ቤተልሔም፡ ኊላ፡ ትበገር፡ ዘንድ፡ አለሽ፤

እስመ፡ እምኔኪ፡ ይወጽእ፡ ንጉሠ፡ እስራኤል፤

ዘሩባቤል፡ ካንቺ ይወለዳልና፡ ከእገሌ፡ አገር፡ እገሌ፡ ደግ፡ ሰው፡ ወጣ፡ እንዲሉ፤ አንድም፡ ባንቺ፡ ይነግሣልና፤

ወፍናዊሁኒ፡ ዘእምፍጥረተ፡ ዓለም፤

ተስፋ፡ መንግሥቱ፡ ከጥንት፡ ጀምሮ፡ የተነገረ፤ ኢይወጽእ፡ ምስፍና፡ ወምልክና፡ እም አባሉ፡ ለይሁዳ፡ እንዲል፤

፫፤ በእንተ፡ ዝንቱ፡ ትሁቦሙ፡ እስከ፡ ጊዜ፡ ትውልደ፡ ትውልድ፤

ተማርከው፡ የሚመለሱ፡ ስለ ሆነ፡ እስከ፡ ልጅ፡ ልጅ፡ ዘመን፡ ተስፋ፡ ሚጠትን፡ ትሰጣቸዋለህ፤

ወእለ፡ ተርፉ፡ አኃዊሆሙ፡ ይትመየጡ፡ ኀበ፡ ደቂቀ፡ እስራኤል፤

ዐሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀሩ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ ወደ፡ ዐሥሩ፡ ነገድ፡ ይመለሣሉ፤

፬፤ ወይቀውም፡ ወይሬኢ፡ መርዔቶ፡ በኃይለ፡ እግዚአብሔር፤

ዘሩባቤል፡ ይነግሥላችኋል፤ በእግዚአብሔር፡ ኃይል፡ እስራ ኤልን፡ ይጠብቃል፤

ወእግዚአብሔር፡ አምላኮሙ፡ ይሄሉ፡ ምስሌሆሙ፤

ፈጣሪያቸው፡ እግዚብሔር፡ በረ ድኤት፡ ከሳቸው፡ ጋራ፡ ይኖ ራል፤ አንድም፡ ወአንቲኒ፡ ቤተልሔም፡ ብለህ፡ መልስ፤ አንቺም፡ ቤተልሔም፡ ኊላ፡ ትበገር፡ ዘንድ፡ ዛሬ፡ አንሰ ሻል፤ እስራኤል፡ ዘነፍስን፡ የሚጠብቅ፡ ጌታ፡ ባንቺ፡ ይወ ለዳልና፤ ልደቱ፡ ቅድመ፡ ዓለም፡ የታወቀ፡ ልደት፡ ቀዳማዊ፡ ተዓውቀ፡ በደኃራዊ፡ ልደት፡ እንዲል፤ ሰው፡ ሁነህ፡ ሥጋ፡ ለብሰህ፡ የምታድናቸው፡ ስለ ሆነ፤ ለልጅ፡ ልጅ፡ ዘመን፡ ሚጠተ፡ ነፍስን፡ ትሰጣቸዋ ለህ፤ ከእንቢታ፡ ከክህደት፡ የቀሩ፡ አሕዛብ፡ ወደእስራኤል፡ ዘነፍስ፡ ይመለሳሉ፤ ክርስቶስ፡ ሰው፡ ይሆናል፤ በእግዚአብ ሔርነቱ፡ ኃይል ጌታ፡ ምእመ ናንን፡ ይጠብቃል፤ ፈጣሪያ ቸው፡ እግዚአብሔር፡ አድሮባ ቸው፡ ይኖራል፤



እስመ፡ ናሁ፡ ይእዜ፡ የዓብዩ፡ አፉሆሙ፡ እስከ፡ አጽናፈ፡ ምድር፤

እነ፡ ሰናክሬም፤ አንድም፡ እነ ናቡከደነፆር፡ ቃላቸውን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አድርገው፡ ይናገራሉና፤ ሰናክሬም፡ ቦኑ፡ ግልፎ፡ ዘያድ ኅን፡ በኢየሩሳሌም፡ ብሎ፤ ናቡ ከደነፆር፡ አነ፡ ውእቱ፡ ዘአሠ ርቅ፡ ፀሐየ፡ ብሎ፡ ተናግሯልና፤

፭፤ ወትከውን፡ ዛቲ፡ ሰላም፡ አመ፡ መጽአ፡ ፋርስ፡ ውስተ፡ ምድርክሙ፡ ወአመ፡ ዐርገ፡ ውስተ፡ ብሔርክሙ፤

እለ፡ ሰናክሬም፡ ወደሀገራችሁ፡ በዘመቱ፡ ጊዜ፡ ያች፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ትደረግላችኋለች፤

ወይትነሥኡ፡ ፯ቱ ኖሎት፡ በላዕሌሁ፡ ወ፰ቱ፡ ሠራዊት፤

ሰባቱ፡ ሊቃነ፡ መላእክት፡ ስም ንተኛ፡ ሠራዊተ፡ ዲያብሎስ፡ ይነሡበታል፤

፮፤ ወይሬእይዎ፡ ለአሶር፡ በኩናት፤

ሥላሴ፡ ሰናክሬምን፡ በፀብ፡ ዓይን፡ ያዩታል፤

ወለምድረ፡ ናምሩድ፡ በውስተ፡ ኀዘኢቱ፡

ዘኩነና፡ ዘቀነያ፡ ያለበት፡ ነው፤ በከተማ፡ ሆኖ፡ የናምሩድን፡ ዕፃ፡ የሚገዛ፡ ሰናክሬምን፡ በዓይነ፡ መዓት፡ ያዩታል፤ አንድም፡ ወለወልደ፡ ናምሩድ፡ በውስተ፡ ኀዘዓቱ፡ ይላል፤ አንድም፡ እስመ፡ ናሁ፡ ይእዜ፡ የዓብዩ፡ አፉሆሙ፡ እስ፡ ብልጣሶር፤ የእስ ራኤል፡ ፈጣሪ፡ አያድን፡ አይ ራዳ፡ ይላሉና፤ ይች፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ስትሩፋን፡ ትሆናለች፤ አመ፡ ወጽኡ፡ ሲል፡ ነው፤ እለ፡ ቂሮስ፡ እለ፡ ዳርዮስ፡ ወደሀገ ራችሁ፡ በዘመቱ፡ ጊዜ፡ ትክ ውን፡ ላለው፡ ስለኖሩባት፡ ባቢ ሎንን፡ ስትሩፋን፡ ብሔርክሙ፡ አላት፤ ይትነሥኡ፤ ሰባቱ፡ ነገ ሥታት፡ ስምንቱ፡ እልፍ፡ ሠራዊት፡ ስለቂሮስ፡ ረዳት፡ ሁነው፡ ይነሣሉ፤ ብልጣሶርን፡ በፀብ፡ ዓይን፡ ያዩታል፤ ዘቀ ነያ፡ ዘኩነና፡ ያለበት፡ ነው፤ አይለወጥም፤ አንድም፡ ወለወ ልደ፡ ናምሩድ፤ ሲል፡ የናም ሩድ፡ ልጅ፡ ብልጣሶርን፡ በፀብ፡ ዓይን፡ ያዩታል፤ ቂሮስ፡ ዳር ዮስ፡ ወደባቢሎን፡ በዘመቱ፡ ጊዜ፡ ከብልጣሶር፡ ትድናላችሁ፡ አለ፤ አንድም፡ እስመ፡ ናሁ፡ ይእዜ፡ የዓብዩ፡ አፉሆሙ፡ ብለህ፡ መልስ፤ ዲያብሎስ፡ አነ፡ ፈጣሪሆሙ፡ ለእሉ፡ ፍጡራን፡ እያለ፡ ቃሉን፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አድ ርጎ፡ ይናገራል፤ ሰብአ፡ ሰገል፡ ወደሀገራችሁ፡ በመጡ፡ ጊዜ፡ ይህች፡ ተድላ፡ ደስታ፡ ትደረ

www.ethiopianorthodox.org

ግላችኋለች፣ ሰባቱ፡ ነገሥታት፡ ስምንተኛውን፡ ሠራዊት፡ ይዘው፡ ይነሣሉ፣ እስራኤል፡ ከሰብአ፡ ሰገል፡ አንዱንም፡ አንዱንም፡ በፀብ፡ ዓይን፡ ያዩታል፣ ሲወጉን፡ መጡ፡ ይኋቸዋልና፣ በከተማ፡ ሆኖ፡ የናምሩድን፡ ዕጣ፡ የሚገዛ፡ አንዱንም፡ አንዱንም፡ በፀብ፡ ዓይን፡ ያዩታል፣ ስንክሳር፡ ሦስት፡ ነገሥታት፡ ሦስት፣ ሠራዊት፡ ገበሩለት፡ ይላል፣ ከዚህ፡ ሰባት፡ ነገሥታት፡ ስምንተኛ፡ ሠራዊት፡ ገበሩለት፡ አለ፣ አይጣላም? ቢሉ፡ አይጣላም፣ ስምንተኛው፡ ንጉሥ፡ በደዌም፡ ምክንያት፡ እንደሆነ፡ የቀረበት፡ አልታወቀም፣ ሠራዊቱን፡ ሰዶ፡ ቀርቷል፣ ሰባቱ፡ ነገሥታት፡ ስምንተኛውን፡ ሠራዊት፡ ይዘው፡ መንገድ፡ ጀመሩ፣ ያች፡ የፍየል፡ ግምባር፡ የማታህል፡ ኢየሩሳሌም፡ ስንኳን፡ ለናንት፡ ለፈረሳችሁ፡ ለሠረገላችሁ፡ ትበቃለች? ብለዋቸው፡ አራቱ፡ ነገሥታት፡ ስምንተኛውን፡ ሠራዊት፡ ይዘው፡ ተመልሰዋል፣ መነሣታቸውን፡ ሲያይ፡ ደቂቀ፡ ነቢያት፡ ሰባት፡ ነገሥታት፣ ስምንተኛ፡ ሠራዊት፡ ገበሩለት፡ አለ፣ ስንክሳር የገበሩለትን፡ ሲያይ፡ ሦስት፡ ነገሥታት፡ ሦስት፡ ሠራዊት፡ አለ፤

ወትድኅኑ፡ እምአሶር፡ አመ፡ መጽአ፡ ፋርስ፡ ውስተ፡ ምድርክሙ፡ ወአመ፡ ዓርገ፡ ውስተ፡ አድባሪክሙ፣

ምድር፡ አድባር፡ አንድ፡ ወገን፣ እኑ፡ ሰናክሬም፤ አንድም፡ ቂሮስ፡ዳርዮስ፤ አንድም፡ ሰብአ፡ ሰገል፡ ወደሀገራችሁ፡ በመጡ፡ ጊዜ፡ ከመከራ፡ ትድናላችሁ፤

፯፤ ወይከውኑ፡ ተረፈ፡ ያዕቆብ፡ በማዕከለ፡ ብዙኃን፡ አሕዛብ፡ ከመ፡ ጠል፡ ዘይወርድ፡ እምኀበ፡ እግዚአብሔር፣

አሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀሩ፡ ትሩፋን፡ በብዙ፡ አሕዛብ፡ መካከል፡ ከእግዚአብሔር፡ ታዝዞ፡ እንደሚወርድ፡ እንደ ክፉ፡ ጠል፡ ይሆናሉ፤

ወከመ፡ አባግዕ፡ ውስተ፡ ተሐግ፣

አሕዛብ፡ በበግ፡ ፊት፡ እንዳለች፡ ሰርዶ፡ ይሆናሉ፤

ወኢይትመየጥ፡ ፩ዱ፡ እምውስተ፡ ደቂቀ፡ እጓለ፡ እመሕያው፣

ከእስራኤል፡ አንድ ሰው፡ ሳይገድል፡ ሳይማርክ፡ አይመለስም፤ አንድም፡ ከአሕዛብ፡ አንድ፡ ሰው፡ አይቀርም፡ ይጠፋል፤



፰፤ ወይከውን፡ ተረፈ፡ ያዕቆብ፡ ማዕከለ፡ ብዙኃን፡ አሕዛብ፡ ከመ፡ አንበሳ፡ ውስተ፡ እንስሳ፡ በገዳም፣

ዐሥሩ፡ ነገድ፡ ተማርከው፡ የቀሩ፡ ሁለቱ፡ ነገድ፡ በእንስሳ፡ መካከል፡ እንዳለ፡ እንደ፡ አባት፡ አንበሳ፡ ይሆናሉ፤

ወከመ፡ ዕጓለ፡ አንበሳ፡ ውስተ፡ መርዔተ፡ አባግዕ፣

በብዙ፡ በግ፡ መካከል፡ እንዳለ፡ እንደ፡ አንበሳ፡ ወይፈን፡ ይሆናሉ፤

ከመ፡ ሶበ፡ ይመጽእ፡ ወይሠርር፡ ወይመሥጥ፡ ወአልቦ፡ ዘያነግፎ፣

ተወርውሮ፡ መጥቶ፡ በነጠቀ፡ ጊዜ፡ የሚያስጥለው፡ እንደሌለ፤

፱፤ ከማሁ፡ ትትሌዓል፡ እዴከ፡ ዲበ፡ እለ፡ ይሣቅዩከ፣

መከራ፡ በሚያጸኑብህ፡ ሰዎች፡ ላይ፡ ሥልጣንህ፡ ከፍ፡ ከፍ፡ ትላለች፤

ወይዘረዉ፡ ኵሎሙ፡ ፀርከ፣

ጠላቶችህ፡ ሁሉ፡ ይጠፋሉ፤

፲፤ ወይከውን፡ ይእተ፡ አሚረ፡ ይቤ፡ እግዚአብሔር፣

ያን፡ ጊዜ፡ እግዚብሔር፡ እንዲህ ይሆናል፡ አለ፤

እሤርዎን፡ ለአፍራሲከ፡ በማዕከሌከ፣

ይከውን፡ ያለውን፡ እሤርዎን፡ ብሎ፡ አመጣው፤ አሕዛብ፡ ፈረሶችህን፡ እስራኤል፡ በመካከልህ፡ አጠፋቸዋለሁ፣ ሁለት፡ ሰሚ፡ ነው፤

ወአጠፍዕ፡ ሠረገላከ፣

ሠረገላህን፡ አጠፋዋለሁ፤

፲፩፤ ወእሤርዎን፡ ለአህጉረ፡ ብሔርከ፣

ያገርህን፡ አውራጃ፡ ሁሉ፡ አጠፋለሁ፤

ወእነኅል፡ ኵሎ፡ አጽዋኒከ፣

አምባውን፡ ሁሉ፡ አፈርሰዋለሁ፤ አንድም፡ አርበኞችህን፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፲፪፤ ወእሥዕር፡ ኵሎ፡ ሥራያቲከ፡ እምእደዊከ፣

ሟርትህን፡ ሁሉ፡ ከእጅህ፡ አጠፋለሁ፤

ወአልቦ፡ ዘይትዋሳዕ፡ ለከ፣

አድንሃለሁ፡ ብሎ፡ የሚከራከርልህ፡ የለም፤

፲፫፤ ወእሤሩ፡ ግልፎከ፣

የተቀረፀ፡ ጣዖትህን፡ አጠፋለሁ፤

ወምስለከ፡ እምእደዊከ፣

ጣዖትህን፡ ከእጅህ፡ አጠፋለሁ፤ አንድም፡ መልክህን፡ አጠፋዋለሁ፤

ወኢትሰግድ፡ እንከ፡ ለግብረ፡ እደዊከ፣

ለጅህ፡ ሥራ፡ ለጣዖትህ፡ እንዳትሰግድ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፬፤ ወእገዝም፡ ምህራማቲከ፡ እማዕከሌከ፤

መስገጃህን፡ ከመካከልህ፡ አጠፋዋለሁ፤

ወአጠፍዖን፡ ለአህጉሪከ፤

አገሮችህንም፡ አጠፋቸዋለሁ፤

፲፭፤ ወእገብር፡ በቀለ፡ ውስተ፡ አሕዛብ፡ በመዓትየ፡ ወበመቅሠፍትየ፤

ተቆጥቼ፡ ባመጣሁት፡ መዓት፡ መቅሠፍት፡ በአሕዛብ፡ በቀ ልን፡ አደርጋለሁ፤

እስመ፡ ኢሰምዑኒ፡ ቃልየ፤

ቃሌን፡ አልሰሙኝምና፡፡

## ምዕራፍ ፮

፩፤ ስምዑ፡ አድባር፡ ቃለ፡ እግዚ አብሔር፡ እግዚእ፡ ዘይቤ፤

ነገሥታቱን፡ እንዲህ፡ ይላቸ ዋል፤ እግዚአብሔር፡ የተናገ ረውን፡ ነገር፡ ስሙ፤

ተንሥእ፡ ተዋቀሶሙ፡ ለአድባር፤

ተነሥተህ፡ ነገሥታቱን፡ ተከ ራከራቸው፡ ያለውን፡ ስሙ፤

ወይስምዑ፡ አውግር፡ ቃለከ፤

መኳንንቱም፡ ነገርህን፡ ይስሙ፤ አንድም፡ እንዲህ፡ ያለውን፡ ስሙ፤

፪፤ ስምዑ፡ አድባር፡ ቅስተ፡ እግ ዚአብሔር፤

ነገሥታቱ፡ የእግዚአብሔርን፡ ነገር፡ ስሙ፤

ወቴላተ፡ መሠረተ፡ ምድርኒ፤

የትሑታኑ፡ መገኛ፡ የሚሆኑ፡ የነገሥታቱ፡ ቋሚ፡ ለጓሚ፡ ይስሙ፤

እስመ፡ ይትዋቀሦሙ፡ እግዚአብሔር፡ ለሕዝቡ፡ ወይዛለፎሙ፡ ለእስራኤል፤

እግዚአብሔር፡ ወገኖቹን፡ ይዋቀሳቸዋልና፤

፫፤ እንዘ፡ ይብል፡ ሕዝብየ፡ ምንተ፡ ረሰይኩከ፤

ወገኔ፡ ምን፡ አደረግኩህ፡ ብሎ፤

ወምንተ፡ አተከዝኩከ፤

ምን፡ አሳጥቼ፡ አሳዘንኩህ፤

ወምንተ፡ አጽሐብኩከ፤

ምን፡ ስጠኝ፡ ብዬ፡ አስቸ ገርኩህ፤

ንግረኒ፤

እስቲ፡ ንገረኝ፤

፬፤ ናሁ፡ አውጻእኩከ፡ እምድረ፡ ግብፅ፤

እነሆ፡ ከግብፅ፡ አወጣሁህ፤

ወባላህኩከ፡ እምቤተ፡ ቅኔ፤

ከጽኑ፡ አገዛዝ፡ አዳንሁህ፤

ወፈነውኩ፡ ቅድሜከ፡ ሙሴሃ፡ ወአሮ ንሃ፡ ወማርያምሃ፤

ሙሴን፡ መስፍን፡ አሮንን፡ ካህን፤ ማርያምን፡ የሴት፡ አለቃ፡ አድርጌ፡ በፊትህ፡ ሰደድሁልህ፤



፭፤ ተዘከር፡ ሕዝብየ፡ ዘመከረ፡ ላዕሌከ፡ ባላቅ፡ ንጉሠ፡ ሞዓብ፤

ወገኔ፡ እስራኤል፡ የሞዓብ፡ ንጉሥ፡ ባላቅ፡ ወልደ፡ ሴፎር፡ ባንተ፡ ላይ፡ የመከረውን፡ ምክር፡ አስብ፤

ወምንተ፡ አውሥኦ፡ ለበለዓም፡ ወልደ፡ ቢዖር፡ እምስኪኖን፡ እስከ፡ ገልገላ፤

ከሰኪኖን፡ እስከ፡ ገልገላ፡ ድረስ፡ በዘተኀ፡ በሰፈርህ፡ ጊዜ፡ ባላቅ፡ ወልደ፡ ሴፎር፡ የቢዖር፡ ልጅ፡ በለዓምን፡ ምን፡ ዓለው? ረግመህ፡ አጥፋልኝ፡ ያለው፡ አይደለም? አንድም፡ ምንት፡ አውሥኦ፡ በለዓም፡ ለባላቅ፤ የቢዖር፡ ልጅ፡ በለዓም፡ ባላ ቅን፡ ምን፡ አለው? ረግመህ፡ አጥፋልኝ፡ ቢለው፡ እግዚአ ብሔር፡ ያልረገመውን፡ ምን፡ ብዬ፡ እረግመዋለሁ፤ ከነገሥ ታት፡ ከመኳንንት፡ በላይ፡ አየ ዋለሁ፡ እንጂ፡ አላስወግምን፤

ከመ፡ ይትዓወቅ፡ ጽድቁ፡ ለእግዚአብሔር፤

የእግዚአብሔር፡ ቸርነቱ፡ ይታ ወቅ፡ ዘንድ፤ ባላቅ፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ተናግሮ፡ እግዚአብሔር፡ ያላዳናቸው፡ ቢሆን፡ የእግዚ አብሔር፡ ቸርነቱ ባልታወቀም፡ ነበርና፤

፮፤ ወስእመቦ፡ ዘይብለከ፡ በምንትኑ፡ እንከ፡ እንጋ፡ እረክቦ፡ ለእግዚአብሔር፤

እግዚአብሔርን፡ ምን፡ ባደርግ፡ አገኘዋለሁ፡ የሚል፡ ሰው፡ ቢኖር፤

ወእትዌከፎ፡ ለአምላኪየ፡ ልዑል፤

ልዑል፡ የሚሆን፡ ፈጣሪዬን፡ በምን፡ እቀበለዋለሁ፡ የሚልህ፡ ቢኖር፤

ጉባዔ፤

እረክቦኑ፡ እንጋ፡ ለእግዚአብሔር፡ በመ ሥዋዕተ፡ አልህምት፡ ዘዓመት፤

እንደ፡ ዳዊት፤ እንደ፡ ሰሎ ሞን፡ ቀንዱ፡ ያልከረከረ፡ ጠጉሩ፡ ያላረረ፡ የሰባ፡ የወፈረ፡ ላም፡ ብሠዋ፡ አገኘዋለሁ? ቢልህ፤

፯፤ ወእትዌከፍኑ፡ እንጋ፡ እግዚ አብሔር፡ በ፱፻ አባግዕ፤

እንደ፡ ኢዮስያስ፡ እልፍ፡ በግ፡ ብሠዋ፡ አገኘዋለሁ? ቢልህ፤

ወእመ፡ አኮ፡ በበኵርየ፡ በፍሬ፡ ከር ሥየ፡ በእንተ፡ ኃጢአትየ፡ ወበጌጋየ፡ ነፍስየ፤

ይኸም፡ ባይሆን፡ ስለፍጹም፡ ኃጢአቴ፡ እንደ፡ ዮፍታሄ፡ የበ ኸር፡ ልጄን፡ ብሠዋ፡ አገኘዋለሁ? ቢልህ፤

ወእመ፡ አኮ፡ በአዕላፍ፡ ሐራጊት፡ ስቡሐን፤

ይኸም፡ ባይሆን፡ እንደሙሴ፡ እንደ፡ አሮን፡ ብዙ፡ ጊደር፡

www.ethiopianorthodox.org

ብሠዋ፡ አገኘዋለሁ? የሚልህ፡ ሰው፡ ቢኖር፤

፰፤ እመቦ፡ ዘይቤለከ፡ በምንትኑ፡ እንጋ፡ እረክቦ፡ ለእግዚአብሔር፤

ከዚህ፡ ሁሉ፡ እግዚአብሔርን፡ በምን፡ አገኘዋለሁ፡ የሚልህ፡ ሰው፡ ቢኖር፤

በሎ፡ ምንተ፡ ይፈቅድ፡ እምኔከ፡ እግዚአብሔር፤

እግዚአብሔር፡ ካንተ፡ ምን፡ ይሻል፡ በለው፤

ዘእንበለ፡ ከመ፡ ትግበር፡ ጽድቀ፡ ወታፍቅር፡ ምጽዋተ፤

በጎ፡ ሥራ፡ ትሠራ፡ ዘንድ፡ ምጽዋት፡ ትመጸውት፡ ዘንድ፡ ነው፡ እንጂ፤

ወትኩን፡ ጥቡዓ፡ ከመ፡ ትትልዎ፡ ለእግዚአብሔር፡ አምላክከ፤

ፈጣሪህ፡ እግዚአብሔርን፡ በሕግ፡ በአምልኮት፡ ለመከተል፡ በአእምሮ፡ የጸናህ፡ ትሆን፡ ዘንድ ነው፡ እንጂ፤

፱፤ ወቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ትሰማዕ፡ በሀገርከ፤

በሀገርህ፡ ቃለ፡ እግዚአብሔርን፡ ትሰማ፡ ዘንድ፡ ነው፡ እንጂ፡ ካንተ፡ ሌላ፡ ምን፡ ይሻል? በለው፤

ወትፍራህ፡ ስሞ፡

ስሙን፡ ትፈራ፡ ዘንድ፡ ነው፡ እንጂ፡ ካንተ፡ ሌላ፡ ምን፡ ይሻል? በለው፤

እስመ፡ ውእቱ፡ ያድኅኖሙ፡ ለእለ፡ ይፈርሁ፡ ስሞ፤

ስሙን፡ የሚፈሩትን፡ እሱ፡ ያድናቸዋልና፤

፲፤ ስማዕ፡ ሕዝብየ፤

ወገኔ፡ እስራኤል፡ ስማ፡

መኑ፡ ይሬሲ፡ እሳተ፡ ውስተ፡ ቤተ፡ ዓማፅያን፡ ዘእግዚአብሔር አኀብረ፤

እግዚአብሔር፡ ያላዘዘውን፡ በበደለኞች፡ መዓት፡ መቅሠፍት፡ የሚያመጣ፡ ማነው፤

እለ፡ ይዘግቡ፡ መዛግብተ፡ ዓመፃ፡ ወቀኖናማተ፡ መዳልወ፡ ተምያን፤

ግብዝ፡ ሚዛን፡ ያለበት፡ የእቃ አቁማዳ፡ የሚያደልቡ፡ ማለት፡ ልቡናቸው፡ ኃጢአትን፡ የተመላ፡ ነው፤

እለ፡ መልዕዎ፡ ለብዕሎሙ፡ በዓመፃ፤

የሰውን፡ ገንዘብ፡ እየቀሙ፡ ባለጸግነታቸውን፡ የመሉ፡ ናቸው፤

፲፩፤ ወእለሂ፡ ይነብሩ፡ ውስቴታ፡ ሐሰተ፡ ይትናገሩ፤

በውስጧ፡ የሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ሐሰት፡ ይናገራሉ፤

ወልሳኖሙኒ፡ ዘጕኅሉት፡ ውስተ፡ አፉሆሙ፤

ከአፋቸው፤ ከአንደበታቸው፡ የሚነገር፡ ነገር፡ ተንኮል፡ ብቻ ነው፤

፲፪፤ ወአነሂ፡ እእኅዝ፡ እቅትልከ፡ ወአጥፍዕከ፡ በእንተ፡ ኃጢአትከ፤

እኔም፡ ስለ፡ ኃጢአትሽ፡ አጠፋሽ፡ ዘንድ፡ እጀምራለሁ፤



፲፫፤ ትበልኢ፡ ወኢትፀግቢ፤

ይህ፡ ሲመጣብሽ፡ ትበያለሽ፡ አትጠግቢም፤

ወይጸልመኪ፡ ብርሃንኪ፤

ተድላሽ፡ ደስታሽ፡ ይጠፋል፤

ትመውቲ፡ ወኢትሐይዊ፤

ትሞቻለሽ፡ እንጂ፡ አትድኚም፤

፲፬፤ ወኵሎሙ፡ ደቂቅኪ፡ እለ፡ ድኅኑ፡ እምኵናት፡ ይወድቁ፡ በረኃብ፤

ከጦር፡ የዳኑ፡ ልጆችሽ፡ በረኃብ፡ ያልቃሉ፤

፲፭፤ ትዘርኢ፡ ወኢትአርሪ፤

ትዘሪያለሽ፡ አትለቅሚም፤

ትተክሊ፡ ዘይተ፡ ወኢትትቀብኢ፡ ቅብዐ፤

ዘይቱን፡ ትተክሊያለሽ፡ አትቀቢም፤

ትተክሊ፡ ወይነ፡ ወኢትሰትዪ፡ ወይነኪ፤

ወይን፡ ትተክሊያለሽ፡ ወይንሽን፡ አትጠጭም፤

፲፮፤ ወይማስን፡ ሥርዓቶሙ፡ ለሕዝብየ፤

የወገኖቼ፡ ሥርዓተ፡ መንግሥት፡ ሥርዓተ፡ ክህነት፡ ይጠፋል፤

ወአቀብኪ፡ ሕጎ፡ ለዘንበሪ፤

የዘንበሪን፡ ሕግ፡ ሥርዓት፡ ጠብቀሻልና፡ ማለት፡ ጣዖት፡ አምልከሻልና፤

ወኵሎ፡ ምግባረ፡ ቤተ፡ አክዓብ፤

የአክዓብን፡ ወገኖች፡ ሥራ፡ ሠርተሻልና፤

ወሖርኪ፡ በምግባሮሙ፡ ከመ፡ ያብዕኪ፡ ውስተ፡ ሙስና፤

ወደጥፋት፡ ያደርስሽ፡ ዘንድ በነዚያ፡ ሥራ፡ ጸንተሻልና፤

ወበእለሂ፡ ይነብሩ፡ ውስቴትኪ፡ ኃሣር፡ ወዕዕለተ፡ አሕዛብ፡ ይረክቦሙ፤

ኃሣረ፡ አሕዛብ፡ ዕዕለተ፡ አሕዛብ፡ ሲል፡ ነው፤ በውስጥሽ፡ የሚኖሩትን፡ የአሕዛብ፡ ስድብ፡ ተዋርዶ፡ ያገኛቸዋል።

## ምዕራፍ ፯

፩፤ አሌ፡ ሊተ፡ እስመ፡ ኮንኩ፡ ከመ፡ ዘያስተጋብዕ፡ ሰዊተ፡ ድኅረ፡ ማዕረር፤

ከመከር፡ በኋላ፡ እሸት፡ እንደሚለቅም፡ ሆኛለሁና፤

ወከመ፡ ተቅራም፡ ድኅረ፡ ቀስም፤

ከወይኑ፡ መከር፡ በኋላም፡ ቃርሚያ፡ እንደሚለቅም፡ ሰው፡ ሆኛለሁና፤ ማለት፡ በጎዎች፡ ሰዎች፡ አልቀው፡ ክፉዎች፡ በተነሡበት፡ ወራት፡ ለተነሣሁ፡ ለኔ፡ ወዮልኝ፤

ዘአልቦ፡ አስካል፡ ዘይበልዑ፡ ደቂቅ፤

ልጆች፡ የሚበሉት፡ ፍሬ፡ የለም፡ ማለት፡ የሚማሩት፡ ትምህርት፡ የለም፤

www.ethiopianorthodox.org

፪፤ አሌ፡ ሊተ፡ እስመ፡ ኀልቀ፡ ኄር፡ እምድር፤

ከዚህ፡ ዓለም፡ ደግ፡ ሰው፡ ጠፍ ቷልና፡ ወዮላቸው፤

ወአልቦ፡ ሰብእ፡ ዘያረትዕ፡ ፍትሐ፤

የቀና፡ ፍርድ፡ የሚፈርድ፡ ሰው፡ የለም፤

ኵሉ፡ ይዔምፅ፤

ሁሉ፡ ይበድላል፤

ወኵሉ፡ ያጠውቅ፡ ቢጾ፡ ወያመነድብ፤

ሰው፡ ሁሉ፡ በውስጥ፡ በአፍአ፡ ባልንጀራውን፡ ያስጨንቀዋል፤

፫፤ ወያነሥኡ፡ እደዊሆሙ፡ ለእኩይ፤

እደ፡ ሥጋቸውን፤ አንድም፡ እደ፡ ልቡናቸውን፡ ለክፋት፡ ያነሣሉ፤

መልአክኒ፡ ይስእል፤

አለቃው፡ ይለምናል፤ የቅሚያ፡ መጀመሪያው፡ልመና፡ነውና፤

ወመኰንንኒ፡ ይየውኅ፡ ከመ፡ ይርከብ፡ ፍትወተ፡ ነፍሱ፤

አገረ፡ ገገርውም፡ ልቡ፡ የሚሻ ውን፡ ያገኝ፡ ዘንድ፡ ያለዝባል፤ መልካም፡ በቅሎ፡ ጭነሃል፤ መልካም፡ ጋሻ፡ ይዘሃል፡ ይለ ዋል፤ እሱም፡ ከወደዱት፡ ይው ሰዱት፡ ይለዋል፤

፬፤ ወአጠፍኦ፡ ለበረከቶሙ፤

እንዲህ፡ አድርገው፡ ያጠራቀ ሙትን፡ ገንዘባቸውን፡ አጠ ፋዋለሁ፤

ከመ፡ ብላዕ፡ ዛዔ፡ ዘይበልዕ፡ ዕፀ፤

ከመ፡ ዕፅ፡ ዘይበልያ፡ ዛዔ፡ ሲል ነው፤ ነቀዝ፡ እንደበላው፡ እንጨት፡ ገንዘባቸውን፡ አጠ ፋዋለሁ፤

ወየዓርግ፡ ዳቤ፡ ንዋይ፡ በዕለተ፡ ጽልመት፤

ብል፡ በጨለማ፡ ብቻ፡ የሚ በላ፡ ሆኖ፡ አይደለም፤ ባዩት፡ ጊዜ፡ በልቶት፡ እንዲገኝ፡ ናቡ ከደነፆር፡ አንድ፡ ጊዜ፡ አጥ ፍቷታልና፤

አሌ፡ ለኪ፡ እስመ፡ በጽሐኪ፡ ፍዳኪ፤

መከራ፡ የምትቀበይበት፡ ቀን፡ ደርሷልና፡ ወዮልሽ፤

ዘይእዜ፡ ይበጽሖሙ፡ ገዓር፤

አሁን፡ መከራ፡ ይመጣ ባቸዋልና፤

፭፤ ኢትትአመንዎሙ፡ ለአዕ ርክቲክሙ፡ እንከ፤

እንግዲህ፡ ወዳህ፡ ባልንጀሮቻ ችሁን፡ አትመኗቸው፤

ወኢትትወከልዎሙ፡ ለመላእክት፤

አለቆችንም፡ አትመኗቸው፤

ወእምብእሲትከ፡ ዘውስተ፡ ሕፅንከ፡ ተዓቀብ፡ ከመ፡ ትዕበያ፤

ባጠገብህ፡ ከምትተኛ፡ ከሚስ ትህም፡ ኃጢአት፡ ሥራ፤ ጣያት፡ አምልክ፡ ብትልህ፡ ፈቃዷን፡ ታፈርስባት፡ ዘንድ፡ ተጠበቅ፤



፮፤ እስመ፡ ወልድኒ፡ የኀሥር፡ አባሁ፤

ልጅ፡ በሃይማኖት፡ ምክንያት፡ አባቱን፡ ያዋርዳልና፤ እንደ፡ ፊቅጦር፤

ወወለትኒ፡ ትትነሣእ፡ ዲበ፡ እማ፤

ሴት፡ ልጅም፡ በሃይማኖት፡ ምክንያት፡ በናቷ፡ ላይ፡ በጠላ ትነት፡ ትነሣለች፤ እንደ፡ ጤቅላ፤

ወመርዓትኒ፡ ላዕለ፡ ሐማታ፤

ምራትም፡ በአማቷ፡ ላይ፡ በሃ ይማኖት፡ ምክንያት፡ በጠላት ነት፡ ትነሣለች፤

ወኵሉ፡ ሰብእ፡ ቤቱ፡ ይፃረሮ፡ ለሰብእ፤

ሰውን፡ ቤተሰቦቹ፡ ይጣሉታል፤ ንጉሥ፡ የወደደውን፤ ዘመን፡ የወለደውን፡ አትመስልም? እያሉ፤ አንድም፡ መከራ፡ እቀ በላለሁ፡ ቢል፡ ሕዋሳቶቹ፡ ይፈሩበታል፤ አንድም፡ አም ላክ፡ ወሰብእ፡ የሆነ፡ ክርስቶ ስን፡ ቤተሰቡ፡ ይሁዳ፡ ይጣላዋል፤

፯፤ ወአንስ፡ ዳዕበ፡ እግዚአብሔር፡ አዐርፍ፤

እኔ፡ ግን፡ በእግዚአብሔር፡ አምናለሁ፤

ወእሴፎ፡ ለአምላኪየ፡ ወመድኃኒየ፤

ፈጣሪዬን፡ መድኃኒቴን፡ [illegible]ዋለሁ፤

ወይሰምዓኒ፡ አምላኪየ፤

ፈጣሪዬም፡ ልመናዬን፡ ይሰማኛል፤

፰፤ ወኢይክሉኒ፡ ሰላቀ፡ ለጸላዕትየ፤

ለጠላቶቼ፡ መዘበቻ፡ አልሆንም፤

እመኒ፡ ድኅፅኩ፡ እትነሣእ፤

በመከራም፡ ብሰነካከል፡ በረድ ኤት፡ እነሣለሁ፤

ወእመኒ፡ ነበርኩ፡ ውስተ፡ ጽልመት፡ እግዚአብሔር፡ ያበርህ፡ ሊተ፤

በመከራም፡ ተይገቼ፡ ብኖር፡ እግዚአብሔር፡ ብርሃን፡ ረድኤ ቱን፡ ያበራልኛል፤

፱፤ ተግሣጸ፡ እግዚአብሔር፡ አንሰ፡ ተዓገሥኩ፤

እግዚአብሔር፡ ያመጣብኝን፡ መከራ፡ እኔ፡ ታገሥሁ፤

እስመ፡ አበስኩ፡ ሎቱ፡ እስከ፡ ያጸ ድቀኒ፡ ፍትሕየ፤

ፈርዶ፡ እስኪያከብረኝ፡ ድረስ፡ እሱን፡ በድዬዋለሁና፤

ወይገብር፡ ሊተ፡ ቅስትየ፤

ፀብ፡ ክርክሬንም፡ ያደርግልኛል፤

ወያገብዓኒ፡ ውስተ፡ ብርሃን፤

ወደተድላ፡ ወደ፡ ደስታ፡ ያደርሰኛል፤

ወእሬእያ፡ ለጽድቁ፤

ቸርነቱን፡ ዓያለሁ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፤ ወትሬኢ፡ ጸላዕትየ፡ ወትለብስ፡ ኀፍረተ፤

ለኔ፡ የተደረገልኝን፡ ተድላዬን፡ ደስታዬን፡ ዓይታ፡ ጠላቴ፡ ሐፍረትን፤ ጕስቍልናን፡ እንደልብስ፡ ትለብሳለች፤

እንተ፡ ትብለኒ፡ አይቴ፡ ውእቱ፡ እግዚአብሔር፡ አምላክከ፤

ፈጣሪህ፡ አያድንህ፤ አይረዳህ፡ ወዴት፡ ነው፡ የምትለኝ፡ ታፍራለች፤

ወይሬእያሃ፡ አዕይንትየ፡ ይእዜ፤

ዛሬ፡ ዓይኖቼ፡ ጥፋቷን፡ ያያሉ፤

ወትከውን፡ ከመ፡ ዕንጕን፡ ዘይከይዱ፡ በውስተ፡ ፍኖት፤

በጎዳና፡ እንደሚረግጡት፡ ትቢያ፡ ትሆናለች፤

፲፩፡ ወታጠፍዓኪ፡ ይእቲ፡ ዕለት፤

ዕለተ፡ ዔዋዌ፡ ታጠፋሻለች፤

ወትማስን፡ ሕግኪ፡ ይእተ፡ ዕለተ፤

ያን፡ ጊዜ፡ ሕግሽ፤ ሥርዓትሽ፡ ይጠፋል፤

፲፪፤ ወይትዐጸዋ፡ አህጉርኪ፤

አገሮችሽ፡ በጦር፡ ይዘጋሉ፤

ወይትካፈልዎን፡ ፋርስ፡ ለአህጉርኪ፡ ጽኑዓት፡ እምጢሮስ፡ እስከ፡ ፈለገ፡ ሶርያ፤

ከጢሮስ፡ ጀምሮ፡ በሶርያ፡ እስከ፡ አለው፡ ወንዝ፡ ድረስ፡ ጽኑዓን፡ የሆኑ፡ አገሮችሽን፡ የፋርስ፡ ሰዎች፡ ይካፈሉታል፤

ወእምባሕር፡ እስከ፡ ባሕር፤

እምጽንፍ፡ እስከጽንፍ፡ ሲል፡ ነው፤ ጽንፍ፡ እስከ፡ ጽንፍ፡ ድረስ፤

ወእምአድባር፡ እስከ፡ አድባር፤

ከተራራው፡ እስከ፡ ተራራው፡ ድረስ፡ ይካፈሉታል፤

፲፫፤ ወትማስን፡ ምድር፡ ምስለ፡ ኵሉ፡ ዘይነብሩ፡ እምፍሬ፡ እከየ፡ ምግባሮሙ፤

ስለሥራቸው፡ ክፋት፡ ምድር፡ በሷ፡ ከሚኖሩ፡ ሰዎች፡ ጋራ፡ ትጠፋለች፤

፲፬፤ ረዐይ፡ ሕዝበከ፡ በበትርከ፤

ሕዝቅያስ፡ ዘሩባቤል፡ ወገኖችህ፡ እስራኤልን፡ በሥልጣንህ፡ ጠብቅ፤

ወነገደ፡ አባግዓ፡ ርስትከ፤

ርስት፡ ኢየሩሳሌም፤ አባግዕ፡ አብርሃም፤ ይስሐቅ፤ ያዕቆብ፤ ነገድ፡ እስራኤል፡ በኢየሩሳሌም፡ የሚኖሩ፡ የወገኖችህ፡ የአብርሃምን፤ የይስሐቅ፤ የያዕቆብን፡ ልጆች፡ ጠብቅ፤

ወእለ፡ የኀድሩ፡ በባሕቲቶሙ፤

ጠላት፡ ጠፍቶላቸው፡ አርፈው፡ ይኖራሉ፤

ወይትረአዩ፡ ውስተ፡ ያም፡ ዘማዕከለ፡ ቀርሜሎስ፡ ወባሳን፡ ወገለዓድ፤

በቀርሜሎስና፡ በባሳን፡ በገለዓድ፡ መካከል፡ በዛፉ፡ ሥር፡ ይኖራሉ፤ ብዛታቸውን፡ መናገር፡ [illegible]



በከመ፡ መዋዕለ፡ ዓለም፤

እንደ፡ ዳዊት፡ እንደ፡ ሰሎሞን፡ ዘመን፤

፲፭፤ ወከመ፡ መዋዕል፡ ዘአመ፡ ዓርገ፡ እምግብፅ፤

ከግብፅ፡ እንደወጡበት፡ እንደ፡ ሙሴ፡ እንደአሮን፡ ዘመን፤

ወትሬእዩ፡ መንክረ፤

ድንቅ፡ ነገር፡ ታያላችሁ፤

፲፮፤ ወይሬእዩ፡ አሕዛብ፡ ወይትኀፈሩ፡ በኵሉ፡ ኃይሎሙ፤

አሕዛብ፡ ለእስራኤል፡ የተደረገውን፡ ተአምራት፡ ዓይተው፡ በፍጹም፡ ኃይላቸው፡ ያፍራሉ፤

ወይወድዩ፡ እደዊሆሙ፡ ውስተ፡ አፉሆሙ፤

እጃቸውን፡ ካፋቸው፡ ላይ፡ ይጭናሉ፤ ዝም፡ ይላሉ፤

ወይጠፍሑ፡ እደዊሆሙ፤

በጃቸው፡ ጭናቸውን፡ ይጸፋሉ፡ (ያጨበጭባሉ)፡የብስጭት፡ነው፤

ወይጠይዑ፡ ዕዘኒሆሙ፤

ጆሯቸውን፡ ከመስማት፡ ይመልሳሉ፤

፲፯፤ ወይልሕሱ፡ መሬተ፡ ከመ፡ አርዌ፡ ምድር፤

እንደ፡ እባብ፡ መሬቱን፡ ይልሳሉ፡ ማለት፡ ይዋረዳሉ፤

ወይቀምሑ፡ ሐመደ፤

ፈጽመው፡ ይዋረዳሉ፤

ወይትከወሱ፡ በማዕገቶሙ፤

[illegible] ይጠፋሉ፤

ወይደነግፁ፡ እምእግዚአብሔር፡ አምላክነ፤

ከፈጣሪያችን፡ ከእግዚአብሔር፡ ታዝዞ፡ መከራ፡ ስለመጣባቸው፡ ይደነግጣሉ፤

የዐወይጠ፡ ወይፈርሁ፡ እምኔሁ፤

ከሱ፡ የተነሣ፡ ያዝናሉ፡ ይፈራሉ፤

፲፰፤ መኑ፡ ከማከ፡ አምላክ፡ ዘየአትት፡ ኃጢአተ፤

ላድን፡ ልራዳ፡ ባልህ፡ ጊዜ፡ የዓለሙን ኃጢአት፡ የሚያስተሠርይ፡ እንዳንተ፡ ያለ፡ ፈጣሪ፡ ማነው?

ወኢተዓዱ፡ አበሳሆሙ፡ ለርስቱ፡ ለእለ፡ ተርፉ፡ ወረዙሱ፤

ከሞት፡ የቀሩ፤ በኃጢአት፡ የተዳደፉ፡ የወገኖቹንም፡ ኃጢአት፡ ይቅር፡ የሚል፡ እንዳንተ፡ ያለ፡ ማነው?

ወኢያጸንዕ፡ ስምዓ፡ መዓቱ፤ ሰምዓ፡ መዓቱ፡ ሲል፡ ነው፡ የመዓቱን፡ ምስክር፡ መከራ፡ የሚያጸና፡ ማነው? እንድም፡ ለአምላክነቱ፡ ቀንቶ፡ የሚያመ ጣውን፡ መዓቱን፡ አያጸናም፤

እስመ፡ ፈቃዴ፡ ምሕረት፡ ውእቱ፤

ፈቃዱ፡ ምሕረተ፡ ሲል፡ ነው፡ ምሕረትን፡ የሚወድ፡ ነውና፤

www.ethiopianorthodox.org

አንድም ፈቃዱ፡ ምሕረት፡ ይቅር፡ ባይ፡ ነውና፤

፲፱፤ ይትመየጠነ፡ ወይሣሃለነ፤

ከመዓት፡ ወደ፡ ምሕረት፡ ይመለስልናል፤ ይቅር፡ ይለናል፤

ወያሠጥሞን፡ ለኃጣውኢነ፡ ወይዌር ዎን፡ ውስተ፡ ቀላየ፡ ባሕር፡ ለአበሳነ፤

ትልቁን፡ ጥቃቅኑን፡ ኃጢአታችንን፡ በባሕር፡ ያሰጥመዋል፤ ከባሕር፡ የጣሉት፡ እንዳይታይ፡ አያስብብንም፡ ሲል ነው፤

፳፤ ወትሁብ፡ ጽድቀ፡ ለያዕቆብ፡ ወሣህለ፡ ለአብርሃም፡ በከመ፡ መሐልከ፡ ለአበዊነ፡ በመዋዕለ፡ ትካት፤

ቀድሞ፡ ዘመን፡ ለአባቶቻችን፡ እንደማልህላቸው፤ ለአብርሃም፡ ይቅርታን፤ ለያዕቆብ፡ ቸርነትህን፡ ትሰጣቸዋለህ፤ አንድም፡ ፈቃዱ፡ ምሕረት፡ ድኅነት፡ ዓለምን፡ የሚወድ፡ ነውና፡ ይትመየጠን፡ሰው፡ ሁኖ፤ ሥጋ፡ ለብሶ፡ ከመዓት፡ ወደምሕረት፡ ይመለስልናል፤ ወያሰጥሞን፡ በጥምቀት፤ በሥጋው፤ በደሙ፡ ኃጢአታችንን፡ ያስተሠርይልናል፤ ወትሁብ፤ ለያዕቆብ፡ ዘነፍስ፤ የምግባሩን፡ ዋጋ፡ ትሰጠዋለህ፤ በከመ፡ መሐልከ፡ በሐሙስ፡ ዕለት፡ ብለህ፡ እንደማልህ፡ እንደተናገርህ፤

ተፈጸመ፡ ዘሚክያስ፡ ነቢይ፤

ሚክያስ፡ የተናገረው፡ ነገር፡ ደረሰ፡ ተፈጸመ፤

በረከቱ፡ አምላኩ፡ ትኩን፡ ምስሌነ፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፤

አነቃቅቶ፡ ላስጀመረን፡ አተጋግቶ፡ ላስፈጸመን፡ ለእግዚአብሔር፡ ክብር፡ ምስጋና፡ ይግባው፡ አሜን።

# ዘኢዩኤል ነቢይ፤

## መቅድም

ኢዩኤል፡ ማለት፡ ኅሩይ፡ እግዚአብሔር፤ አንድም፡ ኅሩየ፡ እግዚአብሔር፡ ማለት፡ ነው፤ ነገዱ፡ ከነገደ፡ ሮቤል፡ ነው፤ አባቱ፡ ባቱኤል፤ እናቱ፡ መርሱላ፡ ትባላለች፤ መነሣቱ፡ በኢዮአታም፡ ዘመን፡ ነው፤ ይህ፡ አርእስት፡ ነው፤ ሠለስቱ፡ ምዕት፡ ለመጻሕፍት፡ አርእስት፡ ሲሰጡ፡ አርእስት፡ ሰጥተውታል፤ እርሱ፡ ግን፡ ነገሩን፡ ቃለ፡ እግዝአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ኢዩኤል፡ ወልደ፡ ባቱኤል፡ ብሎ፡ ያመጣዋል፤

## ምዕራፍ ፩

፩፤ ቃለ፡ እግዚአብሔር፡ ዘኮነ፡ ኀበ፡ ኢዩኤል፡ ወልደ፡ ባቱኤል፤

ዘመጽአ፡ ዘተነግረ፡ ሲል፡ ነው፤ ከባቱኤል፡ ልጅ፡ ከኢዩኤል፡ ዘንድ፡ የመጣ፡ የተነገረ፡ የእግዚአብሔር፡ ነገር፡ ይህ፡ ነው፤

፪፤ ስምዑ፡ ዘንተ፡ ሊቃውንተ፡ ቤተ፡ እስራኤል፤

የእስራኤል፡ ወገኖች፡ አለቆች፡ ይኸን፡ ነገር፡ ስሙ፤

ወአፅምዑ፡ ኵልክሙ፡ እለ፡ ትነብሩ፡ ውስተ፡ ምድር፤

በዚህ፡ ዓለም፡ የምትኖሩ፡ ሰዎች፡ ሁሉ፡ ስሙ፤

ለእመ፡ ከዊነ፡ ኮነ፡ ከመዝ፡ በመዋዕሊክሙ፤

በዘመናችሁ፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ተደርጎ፡ እንደሆነ፤

ወበመዋዕለ፡ አበዊክሙ፤

በአባቶቻችሁም፡ ዘመን፡ እንዲህ፡ ያለ፡ ነገር፡ ተደርጎ፡ እንደሆነ፤

፫፤ ከመ፡ ትንግሩ፡ ለደቂቅክሙ፤

እናንተ፡ ለልጆቻችሁ፡ ትነግሩ፡ ዘንድ፤

ወደቂቅክሙኒ፡ ለደቂቆሙኒ፤

ልጆቻችሁም፡ ለልጆቻቸው፡ ይነግሩ፡ ዘንድ፤

ወደቂቆሙ፡ ለካልዕ፡ ትውልድ፤

ልጆቻቸው፡ ለሌላ፡ ትውልድ፡ ይነግሩ፡ ዘንድ፡ አራተኛ፡ ትውልድ፡ ይሆናል፤

፬፤ ዘአትረፈ፡ ዕፄ፡ በልዓ፡ አንበጣ፤

ለእመ፡ ከዊነ፡ ኮነ፡ ያለውን፡ አመጣ፤ ከትል፡ የቀረውን፡ አንበጣ፡ በላው፤

www.ethiopianorthodox.org